ORIGINAL ARTICLE

# A historical analysis of Satiric verses on the administrative history of Gondar Province (1974-1991)

*Ebrahim Damtew*[1]

## *Abstract*

*Although orality and oral culture is predominant in the daily life of the people of Ethiopia, for long the historiogrtaphy of the country has neglected it to comprehend the the people's past. In response of this call ,this study aimed at investigating certain aspects of the history of political and social grievances of the people as reflected in oral verses in Gondar province during (1974-1991). The study is descriptive in nature and employed satire for analysis. The poems were collected through various data collection methods. The main ones are interviews, primary and secondary document analysis. The findings from the poems adhere to leading political personalities in the province, their policies, approaches and the state itself. The dynamic relationship, public reaction to the state policies, grievances, inner feelings, expressions, unheard voices towards the revolution and the Derg were some among others. The continuity of poetic tradition is also reflected in the messages of the poems. The poems are generally shed light about public curiosity, critical observation of the revolutionary reforms and their implementations. For development to occur, it is imperative to involve everyone to participate genuinely in the affair of his / her locality and the country at large. In line with this, the earlier hopes in the revolution are eroded as the civil warwith out clear national picture spread rampantly throughout the nation. The poems reflect the uneasy relation of the state and the wider public at least in Gondar province that ultimately brought about the down fall of the military government and continuity of crisis in the nation.*

**Keywords:** Derg, Ethiopia ,Gondar, opems, satire, social , revolutionary reforms

## አጠቃሎ

በቃል ግጥም ታሪክን ባህልን ከትውልድ ወደ ትውልድ ማስተላለፍ በኢትዮጵያ የተለመደ ባህል ቢሆንም የታሪክ ጥናት ትኩረት ሲሆን ግን እምብዝም አልተስተዋለም። ይህን ከግምት በማስገባት የዚህ ጥናት ዓላማ በጎንደር ክፍለ ሀገር የደርግን ሥርዓት ፖሊቲካዊና ማኅበራዊ ሁነቶችን በተመረጡ ምጸት ለበስ ቃል ግጥሞች ይዘት ተንትኖ ታሪካዊ እንድምታቸውን ማሳየት ነው። ቃል ግጥሞቹ በተለያዩ የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ የተሰበሰቡ ናቸው። መረጃው የተሰበሰበው በዋናነት በቃለ መጠይቅ ሲሆን ፣የመጀመሪያ ደረጃና የሁለተኛ ደረጃ የመረጃ ምንጮችን በመጨመር የመረጃ መደጋገፍ እንዲኖር ጥረት ተደርጓል። ገላጭ የአጠናን ዘዴን በዋናነት በመጠቀም ከተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች የተገኙትን መረጃዎች ለመተንተን ተሞክሯል። የቃል ግጥሞቹ ትንታኔ ትኩረቱ <u>የሥርዓቱን ርዕዮት ዓለም</u>፣ የክፍለ ሀገሩን ከፍተኛ ባለሥልጣናት ከሰፊው ሕዝብ ጋር የነበራቸውን ግንኙነት በወፍ በረር ምን እንደሚመስል ያሳያሉ። በተጨማሪም በሥነቃሎቹ ይዘት ላይ ማኅበራዊ፣ ባህላዊና ኢኮኖሚያዊ ትንተና ለማቅረብ ተሞክሯል። በዚህም የሕዝቡን የላቀ ንቃተ ኅሊናና የመግለጽ ዐቅም ትልቅነት የስላቅ ንግግር ታሪካዊ ቀጣይነትን ለመታዘብ ተችሏል። ባጠቃላይ የጥናቱ ፈትለ ነገር በደርግ ዘመነ መንግሥት በጎንደር ክፍለ ሃገር ፣እንዲሁም በሀገሪቱ የነበረውን ፖሊቲካዊ እና ማኅበራዊ

1 *Department of History and Heritage Management, College of Social Sciences and Humanities, University of Gondar, Email: damtewebrahim@gmail.com*

***This journal is licensed under a creative common Attribution-Noncommercial 4.0. It is accredited to the University of Gondar, College of Social Sciences and Humanities.***

**DOI:** https://dx.doi.org/10.4314/erjssh.v10i2.10

ዘርፍ የመንግሥትና የሕዝብ መሥተጋብር ምሬት አቤቱታ ምን ይመስል እንደ ነበር በተመረጡ የቃል ግጥሞች የመረመረ ሲሆን ፣በዘመኑ የነበረው የሕዝቡ የኑሮ ሁኔታ ሁለንተናዊ ችግሮች በተጠቀሱት ቃልግጥሞች ይዘት ትንተና ላይ ታይቷል። ይህ ቅሬታ ከሌሎች ተመሳሳይ ችግሮች ጋር በመተባበር የደርግን መንግሥት እንዲወድቅ የበኩላቸውን እንደተወጡ ከቃለ ግጥሞቹ ውስጠ መልዕክት መረዳት ይቻላል።

**ቁልፍ ቃላት፤** ጎንደር ፣ ምጸትለበስ ቃል ግጥም፣ ፖለቲካዊ፣ ማኅበራዊ፣ ደርግ አብዮት

## 1. መግቢያ

በክፍለ አህጉራችን አፍሪካም ሆነ በሀገራቸን ኢትዮጵያ በስነቃል ታሪክና ባህልን ከትውልድ ትውልድ ማስተላለፍ የተለመደ ነው። በዚህም ይሆናል በእድሜ የገፉ ሽማግሎች ሲያልፍ ትልቅ የእውቀት ተቋም እንደጠፋ የሚቆጠረው (Vansina, 1981)። ከዚህም የተነሳ የአፍሪካ አህጉር በርካታ የተጻፉና ያልተጻፉ የባህልና የታሪክ ቅርሶች አሏት(ፈቃደ፣ 199፤ደበበ ፣1983፤ ማኅተመሥላሴ፣ 2007 ዓ.ም)። ለምሳሌ፣ ቃላዊ ኪነ ቃልን ብንወስድ በተለምዶ “አልተማረም” የሚባለውን የኅብረተሰብ ክፍል ልሂቅነት የምንታዘብበት ትልቅ የዕውቀት ሀብት ሆኖ እናገኘዋለን። የዘመናዊ ትምህርትን በተመለከተ የተጠኑ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት የሰው ልጅ አእምሮ ለሚያደርገው ፍልስፍና ለጥበብ መራቀቅ ዐይነ ጥላ ከፋች የሆነው መፍትሔ ማንበብና መጻፍ እንደሆነ በርግጠኝነት ትንታኔ ይሰጣሉ (ሁሉም ይማር፣1955፣ ዓ.ም)። ሆኖም እንደ ኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ከሆነ ሕዝቡ በጽሕፈትም፣ በንባብም ሆነ በቃል ጥበብ ይራቀቃል ፤ይፈላሰፋል። በተለይ ብዙኃኑ በስነቃል ታሪኩን፣ ባህሉን፣ ሃይማኖቱን፣ ልማዱን ከትውድ ትውልድ ያስተለልፍበታል። ኃዘን፣ ደስታ፣ ምኞት፣ ፍቅር፣ ድል፣ ሽንፈት፣ ድጋፍ፣ ተቃውሞ ባጠቃላይ የሕይወት ውጣውረድ ይገልጥበታል( ታደለ ፣2014)። በዚህ አጭር ጥናታዊ ጽሑፍ ትኩረት የተሰጠውም ይህንኑ የሀገር ልማድ፤ የማኅበረሰቡ ርእዮት መገለጫ ስለሆነው የቃል ግጥሞችን ይዘት መተንተን ይመለከታል። ጥበቡም ትኩረት የሚያሻውና ድሮ ብቻ ተከውኖ የቀረ ሳይሆን የትውልድ ቅብብሎሽን የሚያሳየን ነው። ሆኖም ባግባቡ የተጠናና የተሰነደ አይመስልም(ፈቃደ፣2004)። የኅብረተሰቡን አዎንታዊ ስሜትና ተግሳጽ የምናገኘው ከዚሁ ጥበብ ነው። አድርባይነትና ወገንተኝነት ስለማይታይበት አስተማሪነቱ ትልቅ መሆኑን በርካታ የመስኩ ምሁራን ይስማማሉ(ዘሪሁን፣2002፤ፈቃደ፣1994; እና ፈቃደ፣1993)። ጥናቱም ይህን ሐሳብ መሠረት በማድረግ የበኩሉን ለማበርከት ሞክሯል። ይህ ምርምር ምጸት ለበስ ግጥም ትንተና ላይ ያተኮረበት ዋናው ምክንያት ለኢትዮጵያ ሕዝብ ከላይ እስከ ታች “ከሊቅ እስከ ደቂቅ” ባህልንና ታሪክን ሚስጥር ባለው ዘዬ መማማሪያ በመሆኑ ነው(እማሆይ ራዱ መረጃ ሰጪ ቦታ ጎንደር ቀን 3/3/2005ዓ.ም፤ ወርቁ ገሰሰ 5/6/2005/ዓ.ም ፤ዝናቡ ወ/ስላሴ 2/3/2007 ዓ.ም፤ ማኅተመስላሴ፣2007)። በተለይ በአፋኝ ሥርዓቶች በግልጽ መናገር የሚያመጣው መዘዝ ከባድ በመሆኑ ብዙውን ጊዜ ኅብረተሰቡ በውስጠ ትርጉም መናገሩን ስለሚመረጥ የደርግን ሥርዓት በዚህ ጥበብ ማየቱን ጥናቱ መርጧል። ከኅብረተሰቡ ለመማር እውነተኛው መንገድ ይኸው በመሆኑም ጭምር ነው። እንደልማድ ሆኖ አነጋገሪና ምስጢራዊ ትርጉም ያላቸውን ሥነ ቃሎች በመቀመር ስለ ማኅበረሰቡ ፖሊቲካዊ፣ ባህላዊና ኢኮኖሚዊ ጉዳዮች ትዝብትን መግለጽ ብልኅነትን፣ ዕውቀትንና አስተዋይነትን ስለሚያሳይ በኢትዮጵያ ሕዝብ ዘንድ ትልቅ ክብር የሚሰጠው ተግባር ነው። ከዚህ ጋር ተያይዞ ጌታቸው ኃይሌ “... ሕዝባችን የሆነውን በቀጥታ ከመናገር ቁጥብ ነው። በቅኔ ደረጃ ሳይቀር በኅብር መናገር ይመርጣል፤ ይደነቃልም። ... አባቶቻችንን በዕውቀት ያበሰለው ትምህርት ቅኔ ... ዜማ ... የመሳሰሉት ናቸው። ” በማለት ለዘርፉ ትኩረት እንደሚገባ ይጠቁማሉ(አክሊሉ፣2017፡3-5)። በተጨማሪም ማኅተመሥላሴ በበኩላቸው፣ “.... የኢትዮጵያ ሕዝብ የተፈጥሮ ችሎታ የምለው ምሳሌውን፣ አማርኛ ቅኔውን፣ተረቱን ፣ቧልቱን፣ እንቆቅልሹን፣ ሽለላውን፣ ፋከራውን ተጠየቅ ልጠየቅ የሚባለውን ጥያቄና መልሱን፣ በላ ልበልሃ የሚባለውን ውርዱን፣ ዘፈኑን፣ ለቅሶውን ይህንና ይህንን የመሰለውን ሁሉ ነው።” (ማኅተመሥላሴ፣2007፡11) በማለት ተስፋፍቶ መጠናት እንዳለበትም በአንክሮ አስገንዝበዋል። አያይዘውም ቅኔ ውስጠ ትርጉም ባላቸው አጫጭር እና በተመረጡ ቃላት ልዩ ልዩ መልእክት ያላቸውን ሀሳቦች ጠቀለል አድርጎ ለተደራሲያን መግለጽ ለኢትዮጵያ ሕዝብ የተለየ ችሎታውና ስጦታው መሆኑን ይገልጻሉ። ከዚሁ ጋር ተያይዞ ጸጋዬ (1999፣

ዓ.ም፡13-14)የስነ ግጥም ወይም ቅኔን ሳቢነትና የመግለጥ አቅም ታላቅነት ሲያስረዳ " …. ሥነ ግጥም … ኅሊናን በኅሊና የመፈተን አቅም ያላት ስትሆን፣ አንዳንዴም ከብቸኝነት ሕልውናችን ውስጥ ብቻ የምትደመጥ ሙዚቃዊ ፊደል ናትና የኑሮን ውትብትብ ጠልቀን ሠርሥረን ገብተን አገኘን የምንለውን ፍሬ ሃሳብ መንጥቀን እምናወጣባት ናት" በማለት ያስረዳናል።

በተመሳሳይ ዜና ማርቆስ(2012፡1) "ቅኔያዊ ጨዋታ …" በተሰኘ መጸሐፋቸው፣ የሀገራችን ሕዝብ በርካታ የቃል ጥበብ ሀብት ባለቤት መሆኑን ገልጸው፣ በዚሁ የቃል ጥበብ የመመራመር፣ የመራቀቅ፣ የማመስጠርና የመፈላሰፍ ሥራ እንደሚሠራበትና በተለያየ አውዶች ላይ የዕውቀትና ክህሎት ማዕድ ማበልጸጊያ ሆኖ የኖረ እንደሆነ ያብራራሉ። ስለሆነም ይህ ጥበብ ትኩረት የሚሻው መሆኑን አበክረው ይገልፃሉ፡፡ ጎሩይ (2001 ዓ.ም፡1) በበኩላቸው የሠምና ወርቅ ግጥም እንዲሁም የኅብር ቅኔ ቋጠሮ በኢትዮጵያ ባህልና ፍልስፍና የተለመደ ሲሆን ታሪኩም ረጅም መሆኑን ጠቁመዋል። አልተማረም የሚባለው ሕዝብ ከላይ በተጠቀሱት የተለያዩ አውዶች ላይ እጥር ምጥን ባሉ ቃላት ቀምሮ በግጥም ስሜቱን መግለጽ የሚያስችል የረቀቀ ባህል እንዳለው ያብራራሉ። ከዚህ በተጨማሪ የቅኔ ባህል በሀገራችን ቀደምት እንደሆነ፣ብሎም በቃል የሚተላለፈው የሀገራችን ሚስጥራዊ የግጥም ልማድ በምርምርና ጥናት የተወለደ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ የሁለንተናችን ምንጭ መሆኑ ታውቆ ትውልዱ ትኩረት ሊሰጠው እንደሚገባ (መጋቤ ሚስጢር ጥዑመልሳን፣2011 ዓ.ም፡I-III) ያብራራሉ።

ከላይ እንደተገለጸው በሀገራችን የቃል ግጥም የተለያዩ መልዕክትን ሳቢና አመራማሪ በሆነ መልኩ በቃል ለታዳሚ የሚያስተላልፍ ጥበብ ነው፡፡ ምጸታዊ አገላለጽ በጽሑፍም ሆነ በሥነ ቃል ውስጥ ከሚታዩት የሰው ልጅ ኪነጥበባት አንዱ ሲሆን፣ ባብዛኛው መልዕክቱን የሚያስተላልፈው ከሌላው የሥነ ቃል ዓይነት ረቂቅና ሚስጢራዊ በሆነ ውስጠ ታዋቂ መልዕክት አዘል ትርጉም ወይም በተቃራኒው መሆኑን መረጃዎች ያስረዳሉ(ታደለ፣ 2014፤Frienberg, 1967፤ዘሪሁን፣ 2002 እና ላእከማሪያም ፣2011 ዓ.ም)። የዚህ ሂደት ዓላማ በአንድ ሥርዓት ወይም ማኅበረሰብ ክፍል ውስጥ እርምትና መሻሻልን ማየትና ማሳየት ነው። አደጋ ውስጥ የወደቁ መልካም እሴቶችም እንዳይጠፉ አዎንታዊ ትችት በመስጠት ለሁለንተናዊ የማኅበረሰብ እድገት የሚተጋ እንደሆነ መታዘብ ይቻላል። (ዘሪሁን ፤2002 )።

ቅኔዎች /ሥነቃሎች/ ስላቃዊ ንግግሮች ሲመረመሩ ለተቸገሩ እና ለተበሳጩ ትዕግሥትን፣ ለተመቻቸው መጠንን፣ ወደፊት ለቀደሙ ወደኋላ የመቅረት፣ ወደኋላ ለቀሩት ወደፊት የመቅደም እድልን የሚያሰሙ በሚስጥር የበለፀጉ መማሪያም ማስተማሪም ናቸው (ማኅተመሥላሴ፣ 2007፣ ታደለ፣ 2014፤ ካሣሁን፣ ፳፻፲፫)። የጎንደር ክፍለ ሀገርም በርዕሰ ጉዳያችን ላይ እጅጉን የበለፀገ ነው።

በዚህ መነሻነትም ቀጥለን የምናያቸው ሥነቃሎች ይህን ንድፈ-ሐሳባዊ አስተሳሰብ በተግባር የሚያሳዩ ናቸው ብሎ አጥኝው ያምናል። ጥናቱ በጊዜ ሽፋንም ሆነ በቦታ፣ እንዲሁም በይዘት ሳይቀር ውሱንነት አለው። ለትንታኔ የቀረቡትም ቃል ግጥሞች እንደ ጎንደር ክፍለ ሀገር (አካባቢያዊ ይዘት) ያላቸው ሲሆን፣ አንዳንዴ እንደ ሀገርም ሊቃኙ የሚችሉ ናቸው። ለምሳሌ፤ ሦስት ታላላቅ አብዮታዊ መሪዎችንና ፖለቲካዊ አስተዳደራቸው ላይ ያተኮሩ የሥነቃል ይዘቶች ተደሰዋል። ሁለቱ የጎንደር ክፍለ ሀገርን ሲወክሉ ቀሪው እንደ ሀገር መሪ የሚታዩ ናቸው። በተጨማሪም አብረው ሊዳሰሱ የሚችሉ ተያያዥነት ያላቸው ጉዳዮች ቢኖሩም በጥናቱ ይዘትና መረጃ ውስንነት የተነሣ በዘመኑ ፖለቲካዊና ማኅበራዊ ጉዳዮች ላይ ብቻ በመመርኮዝ በጭብጣቸው መሠረት ለማየት ተሞክሯል።

## 2.የጥናቱ ዓላማ

የጥናቱ ዓላማ በደርግ ዘመነ መንግሥት 1966- 1983 ዓ.ም. የጎንደርን ክፍለ ሀገር ፖለቲካዊና ማኅበራዊ ሁነቶች ምን ይመስሉ እንደነበር የክፍለ ሀገሩ ሕዝብ የታዘበውን በምጸት ለበስ ቃልግጥሞች ይዘት ተንትኖ ታሪካዊ እንድምታቸውን ማሳየት ነው።

## 3.የጥናቱ ዘዴ

ጥናቱ ገላጭ የምርምር ንድፍን መሠረት በማድረግ የተከወነ ሲሆን፣ መረጃዎቹም ከተለያዩ የማኅበረሰብ ክፍሎች ተሰብስበዋል። ለመጥቀስ ያክል፤ ከአዝማሪዎች፣ ከሙሾ አውራጆች፣ የአካባቢውን ታሪክ ከሚያውቁ የዕድሜ ባለጸጋ የማኅበረሰቡ አባላት ጋር ቃለምልልስና ውይይት ተደርጓል። በዘርፉ ከጉዳዩ ጋር ግንኙነት ያላቸውን የመጀመሪያ ደረጃናየሁለተኛ ደረጃ የመረጃ ምንጮችን ለመመርምር ጥረት ተደርጓል፡፡ ምጸት ለበስ ቃልግጥሞቹንም ለመሰብሰብም በተለያዩ ማኅበራዊ ዐውዶች ላይ ለመገኘት ተሞክሯል። ለምሳሌ፤ ድግስ ቤት፣ ለቅሶ ቤት፣ ድግስ ቤት፣ እንዲሁም መሸታ ቤትና በመሳሰሉት በመገኘት መረጃ ለመሰብሰብ ጥረት ተደርጓል። አመራረጣቸውም የተኮር ጅምላ ውይይት እና ለቃለመጠይቅ መጀመሪያ ሙከራ ከተመረጡት ሰዎች በማብራራት ብቃታቸውና በግንዛቤ ብስለት የተሻሉትን በቁልፍ መረጃ ሰጪነት ተጠቅሟል። ጠቋሚ የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ አጥኝው በዋናነት ተጠቅሟል። ዓላማውን መሠረት ያደረጉ ጥያቄዎችን በማዘጋጀት ወደ ተመረጡ መረጃ ሰጪዎች በመሄድ መረጃውን ለመሰብሰብ ተችሏል። በጥንቃቄ የተመረጡት መረጃ ሰጪዎች የምጸትለበስ ግጥሞቹን ግልጽ በማድረግ ረገድ ድርሻቸው የጎላ ነበር። በተሰበሰቡት ግጥሞች ላይም ከተመረጡት ሰዎች ጋር በጥልቀት ውይይት ተደርጎባቸዋል፡፡ እንደየ አስፈላጊነቱም መዛግብትንም ለመጠቀም ተሞክሯል። መዛግብቱን ከቀድሞ የጎንደር ክፍለ ሀገር አስተዳደር ሕንጻ ክፍል አጥኝው አግኝቷል። ከርእሱ ጋር ሊዛመዱ ይችላሉ ተብለው የተለዩትን ዋቢ መጻሕፍትን ጭምር በጥናቱ ለማካተት ጥረት ተደርጓል፡፡ ከተለያየ የመረጃ ምንጭ የተሰበሰበውን መረጃ በመገምገም በተገቢው መንገድ ለመተንተን ተሞክሯል። ባጠቃላይ 36 ያክል ቃል ግጥሞች የተሰበሰቡ ሲሆን፣ በወረቀቱ ውስን ዓላማ ምክንያት 11 ያክሉ ለትንተና ተመርጠዋል። በመጨረሻም ለትንተና እንዲያመች ግጥሞቹ በጭብጥ በጭብጥ በመከፋፈል በገላጭ የትንተና ስልት በሐተታ ቀርበዋል። ጭብጦቹም ሁለት ሲሆኑ፣ ፖሊቲካዊ እና ማኅበራዊ እንድምታ ያላቸው ተብለው ተሰይመዋል።

# 4. ፖለቲካዊና ማኅበራዊ ጉዳዮችን መሠረት ያደረጉ ምጸትለበስ የቃል ግጥሞች ትንተና

## 4.1. ፖለቲካዊ ጉዳዮችን[2]

1. ልጅ ከወለዱ አይቀር ከተንበረከኩ፣
 ዳኛ እንደ ገብረሕይወት ልጅ እንደ መላኩ
(ሽመልስ ፣ ዋኘው ፣ 2006፣ ጎንደር)።

በቁጥር 1 በተመለከተው ግጥም ውስጥ የተገለጹት በጎንደር ክፍለሀገር የደርግ ከፍተኛ ባለሥልጣናት ሻለቃ መላኩ ተፈራና መቶ አለቃ በኋላም ሻለቃ ገብረሕይወት ገብረእግዚአብሔር ከመቶ ሃያ የደርግ አባላት ዝርዝር ውስጥ ስማቸው ተጠቅሶ ይገኛል። ሻለቃ ገብረሕይወት ትውልዳቸው ትግራይ ክፍለሀገር አድዋ አውራጃ ሲሆን፣ ከ1966 ዓ.ም. አብዮት ፍንዳታ በፊት በተለያዩ ቦታዎች በመንግሥት ኃላፊነት ሰርተዋል። ከኤርትራ ክፍለሀገር ፈጥኖ ደራሽ ፖሊስ ወደ ደርግ አባልነት እንደመጡ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ከ1969-1976 ከዚህ ዓለም እስከተለዩበት ጊዜ ድረስ አብዮታዊ እርምጃና ቀይሽብር መሪነታቸው ግንባር ቀደም እንደነበሩ ይነገራል። ከሻለቃ መላኩ ተፈራ ያልተናነሰ ስልጣን እንደነበራቸው ይወሳል (ፈንታሁን፣ 2006 ዓ.ም፤ ቃል መረጃ ሰጪ፣ ዝናቡ ወ/ጊዮርጊስ፣ 4/5/2005)። በጎንደር ከተማና አካባቢው፣ እንዲሁም በደባርቅ ሊማሊሞ፣ ዳባት፣ አይከል፣ ደብረታቦር፣ አዲስዘመን፣ ንፋስመውጫ (ጋይንት) የቀይ ሽብርና አብዮታዊ ሰደድ፣ የመንጥር ዘመቻ፣ ነጻ እርምጃ መሪዎች እንደነበሩ ከቃል አቀባዮች እና ከመዛግብት የተገኙ መረጃዎች ይገልጻሉ ( መረጃ ሰጪ፣ አቶ ተገኘ ወርቁ ፣4/6/2006ዓ.ም.፤ አቶ ወርቁ ገሰሰ፣ 4/5/2005 ዓ.ም.፤ መሐመድ አሊ ጭልጋ/አይከል/ 4/6/2005 ዓ.ም.)።

'ኢትዮጵያ ትቅደም!' የሚባል የእሳት ነበልባል ባለበት ጊዜያዊ ሰይፍ መሳፍንት

2 በዘመኑ በጎንደር ክፍለ ሀገር ከሕዝብ አስተዳደር ጋር የተገናኙትን ጉዳዮች ለማመላከት ነው።

> ዲያቢሎስና ሊቃውንት አርዮስን እያረመ አዲሲቷን ኢትዮጵያ እያስቀደመ በመምጣቱ የነበረው ጨለማ ተገፎ የብርሃን ጭላንጭል ብልጭ አለ። አብዮታችን በደማችን ምርታችን በማረሻችን። የጻድቃንና የኅጣን ማጣሪያ ወንፊት ዐብይ የሆኑትን እንክርዳዶች መለየት ያስፈልጋል.... (ጎ/ክ/ ፊይል ቁጥር 23/ ፣ ጎንደር 1970 ዓ.ም)።

ይህም እውን የሚሆነው "አብዮተኞች" ማለት፤ ደርጎች "አብዮታዊ እርምጃ"፣ "አብዮታዊ መፍትሔ"፣ "አብዮቱን ለማዳን አብዮቱን ማፋፋም"፣ "መመሪያችን ማርክሲዝም ስለሆነ እናሸንፋለን!" የሚባሉትን መፈክሮች መፈጸም ሲቻል ነው የሚል እሳቤ ነበራቸው (ዝነከማሁ፤አቶ ወርቁ ገሰሰና መሐመድ አሊ)። በሌላ በኩል የማርክሲስቶች ኅብረት በሥራ ይተርጎም እየተባለ ግራ የተጋባ የእልቂት ዘመን እንደነበር መረጃዎች ይጠቁማሉ። ከላይ በተደጋጋሚ እንደተባለው ተማሪዎቹም ማርክሲስት ነን ሲሉ ደርግም እንዲሁ ይላል። ለምን ኅብረት መፍጠር አቃታቸው? ከዚህ ጋር ተያይዞ፣ ሥነቃሉ በሐሳብ ልዩነታቸው ምክንያት "በአብዮት" ስም በቀይሽብርና በነጭ ሽብር በተቃራኒ ቆመው የጠፉትን ወገኖችንና አጠቃላይ ኢሰብዓዊ እርምጃዎችን ለማስረዳት ሕዝቡ የተጠቀመበት ድምፅ ይመስላል። አንዳንድ የቃል መረጃ ሰጪዎች የሽብሩ ዋና ዓላማ ያንዱን ወገን ተፈሪነት ለማጉላትና አንባገነናዊ ሥርዓትን ከመገንባት አንጻር የሚታይ ነው ይላሉ (መረጃ ሰጪ፣ ዘላለም፣ መስፍን፣ 2007ዓ.ም.)። በእነዚህ ስንኞችም በአጠቃላይ በሥርዓቱና በግለሰቦቹ ላይ የነበረውን ኢፍትሐዊነት፣ አምባገነናዊነትና ጭካኔን "ከወለዱ አይቀር'' እያለ ተሸሚጦባቸዋል። ሕዝቡ ውስጥ የኖሩት የጥበብ ሰዎች የኅብረተሰቡን ምሬትና አቤቱታ ለሀገር በዚህ መልኩ አሳውቀዋል። ስለዘመኑ ክፋትና ጭካኔ አንድ "የታሪክ" ዐዋቂ የሰሙትንና ያዩትን በቀልድ መልክ እንደሚከተለው ነግረውኛል። አንድ ስማቸው ያልተገለፀ በኢሕአፓ የተጠረጠሩ ግለሰብ የወቅቱን መፈክር "አብዮቱ ግቡን ይመታል" እንዲሉ ተጠይቀው "አብዮቱ ግቡን ይመታል" በማለት ፈንታ ጠያቂዎቻቸውን የበለጠ ያስደሰቱ በማስመሰል "ይጠስቀው!!" /በጣም ይመታው/ በማለት መለሱ (መረጃ ሰጪ፣ እሸቴ አብዱረህማን፣ 2007ዓ.ም፤ አሰበ ነጋሽ)። በሌላ በኩል ደግሞ "አብዮታችን ለሐቀኞች በሩ ክፍት ነው" ተብሎ ሲነገራቸው "እኛም ዘለን ጥልቅ" በማለት አፈናው ምን ያክል የከፋ እንደነበር ለማሳየት ሞክረዋል። በስተመጨረሻም "ኢሕአፓና ኢድዩ ይወድማል!" ሲባል "ለኛም አላህ አለን" በማለት ሥርዓቱን እንደሚቃወሙ ውስጥ ውስጡን አሽሚጠዋል። በሌላ በኩል አንድ ሽህ በጎንደር ከተማ ውስጥ የነበረውን የቀይሽብርና ነጭ ሽብር ጦርነት በማስመልከት የመንግሥት የጸጥታ ኀይሎች ችግሩን መፍታት ስለተሳናቸው "እናንተ የመጣችሁት እውነትም ልታረጋጉ ነው " ነገር ግን መንግሥት የሚዳኘው "በቃሉ ነው! በማለት የቀድሞ የሕዝብ ሥነምግባር እየጠፋ በጠመንጃ መገዛት በዛ ለማለት በነገር ጎሸም አድርገው እንዳለፉ ከጥናቱ ተሳታፊዎች ገለጻ መረዳት ይቻላል (መረጃ ሰጪ፣ እሸቴ አብዱረህማን፣ 2007)።

## 2. በደባርቅ ገብረሕይወት በዳባት አጥናፉ በጎንደር መላኩ፣ አገሩን አቀኑት እየተላላኩ።

ይህንን በቁጥር 2 ላይ የተመለከተውን ግጥም ገጥመዋል የተባሉት ግለሰብ ተጠርተው በጥርጣሬ እንዲጠየቁና "አብዮታዊ እርምጃ" ሊወስድባቸው ሲል፣ ግለሰቡ፣ "ጌታዬ እኔ፤ በደባርቅ ገብረሕይወት በዳባት አጥናፉ በጎንደር መላኩ፣ አገሩን አቀኑት እየተላላኩ" ነው ያልኩ ምን ችግር ተገኘብኝ ለውጡን ይኸው የምናየው ነው ሀገር ልታለሙ ኢትዮጵያን ልታስቀድሙ ድሀውን ወገን ከበዝባዦች ነጻ ልታወጡት ትምህርት ሥልጣኔ ልታመጡ መስሎኝ የምትለፉ? ብለው በማስተባበላቸው ሙሉ ልብስ ተሸልመው ወደ ሀገራቸው ወገራ (ገደብጌ) አካባቢ መመለሳቸውን በጊዜው የነበሩ የቃል መረጃ ሰጪዎች ይናገራሉ (የቃል መረጃ ሰጪ አሰበ ነጋሽ፣ ዘገዬ መኮነን፣ 2006 ዓ.ም)። ገጣሚውም ገደብጌ ከደረሱ በኋላ "ልብሱን ማን አለበስዎ?" ሲባሉ "ምቀኛዬ" በማለት በነገረ ሠሪው ላይ አሽሚጠዋል። በግጥሙም ለመግለጽ የተፈለገው ግለሰቦቹ የዘመኑ አምባገነናዊ ሥርዓት መገለጫ መሆናቸውን ነው። ይሁን እንጂ እዚህ ላይ አንዳንድ በጉዳዩ ላይ ያነጋገርኳቸው ቃል አቀባዮች እንደሚሉት በግራና ቀኝ ተሰልፈው የነበሩት ወገኖች የሀገራቸውን የረጅም ጊዜ ታሪክና መልካም እሴት ሳያጤኑ ስሕተት ሠርተዋል በማለት

ይናገራሉ (እማሆይ ራድ ብዙነህ፣ ወ/ሮ የካባ መኮንን፣ አቶ መስፍን ኃለሥላሴ፣ አሰበ ነጋሽ)። ወታደራዊ ሥርዓቱ ካነሳሱ ችግር ቢኖርበትም ለተፈጠረው የሀገር መመሰቃቀል ሁሉንም ወገኖች የያዛቸው የዘመኑ "ሉላዊው" የሥርነቀል ርዕዮት ዓለም ወረርሽኝን መጠየቅ አለመቻላቸው ትልቁን ቦታ እንደሚይዝ ከትንታኔው መረዳት ይቻላል። በመጠፋፋቱ ሂደት ጎንደር ከተማ ግንባር ቀደም ልትሆን እንደምትችል እሚያወሱ በርከት ያሉ መረጃ ሰጪዎች አጥኝውን አጋጥመውታል። በቀዳሚነት ትጠቀስ ከተባለ እንኳን አዲስ አበባ ብቻ ልትሆን እንደምትችል ይነገራል ( መኳንንት አደም፣ አጋፋሪ አበበ የቃል መረጃ የሰጡበት ቀን 4/3/2006 ዓ.ም.፤ እማሆይ ራዱ ብዙነህ የቃል መረጃ የሰጡበት ቀን 21/2/2005 ዓ.ም.)። ይህን ሁኔታ ሕዝቡ በተቃራኒ "አለማችሁ'' ወይም "አቀናችሁ'' /መልካም ሥራ ሠራችሁ/ በማለት የዘመኑን ሁኔታ በተገላቢጦሽ ይጠቁማሉ።

## 3. ላሚቱም ታለበች ግሬራ ግሬራ[3] በሬው ሻኛ አወጣ፣ ገብረሕይወት የሚባል ድንቅ እረኛ አግኝታ፡፡

በቁጥር 3 ላይ የተጠቀሰው ግጥም የሻለቃ ገብረሕይወትን የስሜን አውራጃ አስተዳዳሪንና የጎንደር ክፍለሀገር የጦር ኃይል አዛዥ የነበሩ ሲሆን ይህ ግጥም የሳቸውን አስተዳደር ይመለከታል። ሻለቃው በሬ ሻኛ የሚያወጣው፣ ላም በግሬራ ሙሉ የምትታለበው የመስኩ ሣር፣ ውኃው፣ ድርቆሹ፣ ገለባውና ጭዱ ሲመቻቸው መሆኑ አያጠያይቅም። የተጠቀሱትን ግብዓቶች የሚያቀርብ ታታሪ ጠባቂም ያስፈልጋቸዋል፤ "የከብት አገሩ ባለቤቱ፣ የሰው አገሩ ምግባሩ" እንደሚባለው ማለት ነው። ይህ ሲሆን ምርት ይጨምራል፤ እንስሳቶቹም ደስተኞችና ጤናማ ይሆናሉ። ኑሮው የተመቸው በሬ ሻኛማ፣ እንዲሁም ላሟ ወተታማ (ግታም) ተብለው የተመሰሉት በመቶ አለቃ ገብረሕይወት የሚተዳድረው ሕዝብ ነበር። ለምሳሌ፤ ወገራ፣ ጭልጋና ሌሎቹም የቀድሞ ጎንደር ክፍለሀገር አካባቢ ሕዝብ የሚያጠቃልል ሲሆን፣ የሺ አለቃው አስተዳደር እንደ "ድንቅ እረኛ" ተወስዶ በተገላቢጦሽ ሕዝቡን የተረጋጋና የፈንጠዝያ ሕይወት ውስጥ እንዳኖረው በማስመሰል የአስተዳዳሪው ዘመን በደርግ ወታደራዊ መንግሥት ከታዩት ፈላጭ ቆራጭ፣ ማን አለብኝ ከሚሉት ወታደሮች በግንባር ቀደም የሚጠቀስ ሰው መሆኑን ለመዘከር የተገጠመ እንደሆነ ከቃል አቀባዮች ትንተና መረዳት ይቻላል (መረጃ ሰጪ፣ ወርቁ ገሠሠ፣ ከማል ሙስጠፋ)። በተጨማሪ የሻለቃው ዘመን የተጣላ የሚታረቅበት፣ የተጎዳ የሚካስበት፣ ይቅር ለእግዚአብሔር የሚባባልበት ሥነሥርዓትና ምቾት ለሕዝብ የነበረበት እያስመሰለ ዘመኑ የፍርሃትና የሽብር ጊዜ ሰው <u>የራሱን ጥላ</u> እንኳን ለማመን የማይችልበት ዘመን መሆኑን ለመግለጽ የተቋጠረ ግጥም መሆኑን መረጃ አቀባዮች ያስረዳሉ። ሻለቃ ገብረሕይወት ከክፍለ ሀገሩ አስተዳዳሪ ሻለቃ መላኩ የበለጠ የሚወገዝ የደርግ ከፍተኛ አመራር እንደነበረ መረዳት ይቻላል ( አበበ አየለ ፣ይርጋ የቃል መረጃ የሰጡበት ቀን 4/3/2006ዓ.ም.፣ የቃል መረጃ የሰጡበት ቀን 21/2/2005 ዓ.ም)። ሕዝቡም ከአብራኩ የወጡትን ልጆች ሳይወድ በግድ ዐይኑ እያየ ያለፍርድ ሲገደሉበት እንደነበር ያመለክታል ( ዝነከማሁ)። እዚህ ላይ የዳዋ ም/ወረዳ አስተዳደር አካባቢ ሕዝብ 1974 መንግሥት ፀረ አቢዮተኛች ከሚላቸው ኢሕአፓና ኢድዩ ለማሰስ በሚል ሽፋን በወቅቱ የጎንደር ክፍለ ሀገር የበላይ የፀጥታ ተቆጣጣሪ ኮሚሳሪያት በነበረው ሻለቃ ገብረ ሕይወት ገብረእግዛብሔር ሥምሪት ሰጪነት በተካሄደው አሰሳ የመንግሥት ወታደርና የአካባቢ ሚኒሻ በአካባቢው ሕዝብ ላይ ያደረሰው ግፍና በደል በአቤቱታ አቅራቢዎቹ አንደበት "…. ከሁለት ያጣ ጎመን ሆነን ተዘረፍን ተንገላታን…" የአዝመራ ወቅት አለፈብን አቤቱታችንን ሰሚ አጥተን…" በማለት ይገልጹታል። በአውራጃ ደረጃ ሰሚ አጥተው ወደ ክፍለ ሀገሩ ዋና አስተዳዳሪ የጻፉት የአቤቱታ ማመልከቻ ሁኔታውን ምን ያክል ለገበሬው አስቸጋሪ እንደነበር ይነግረናል።የዳዋ ም/አስተዳደር ሥር የሚኖረው ሕዝብ የአቤቱታ ደብዳቤ ለጎንደር ክፍለሀገር አስተደደር ጽ/ቤት ቀን 10/4/1974 ዓ.ም፤ በተጨማሪ ፣ ሻለቃ ገብረሕወት ገብረ እግዚአብሔር የጎንደር ክፍለ ሀገር ወታደራዊ ኮሚሳር ለ ብ/ጀነራል ስዩም መኮንን የማእከላዊ ኮሚቴ አባልና የወታደራዊ ኮሚሳሪያት ዋና ኃላፊ የተጻፈ ደብዳቤ፣ ቁጥር ፣ወኮ 24ዘጠ/363 ቀን 6/4/1976 ዓ.ምን መመልከት ይቻላል።

3 በጎንደር ግሬራ ማለት የወተት ማለቢያ ዙሪያውን የተቀመቀመ ቅል ሲሆን፣ በሸዋና ወሎ ጮጮ ወይም አኮሌ አኾሌ ይባላል።

4. እናንት ጎንደሬዎች ሰው ጥሩ እባካችሁ፣
አንድ መላኩነው ያሳለፈላችሁ።
5. ወጪ ወራጅ ከማየት ቆሞ ከመንገድ፣
እንደመሳዕኩ ነው መሄድ መራመድ (አበበ አየለ)።

የአንድ መንግሥት ሥርዓት አጠቃላይ ሁኔታ በመሪዎች ተግባር ላይ ይመሰላል። የነሻለቃ መላኩም ዘመን ከጊዜው ጋር የሚታይ ነው። ሻለቃ መላኩ ተወላጅነታቸው እና እድገታቸው በጎንደር ክፍለሀገር በደብረታበር አውራጃ ፋርጣ ወረዳ ሲሆን፣ ኢትዮጵያን ለመምራት ከተሰበሰቡት መቶ ሃያ የደርግ አባላት ዝርዝር ውስጥ ስማቸው ተጽፎ ይገኛል። የተመረጡትም ከምድር ጦር ሁለተኛ ብርጌድ እንደሆነ ይነገራል። ረጅም የሚባል ጊዜ በጎንደር ክፍለ ሀገር በአስተዳዳሪነት ሰርተዋል። እንደሚታወቀው ዘመኑም ብዙ ውጣ ውረዶች የበዙበት ወንድም ወንድሙን የሚያጠፋበት "ኅብረተሰባዊነት" የተሰኘ ያስተዳደር ዘመን ነበር (ፈንታሁን፣ 2006 ዓ.ም)። ሻለቃ መላኩ የጎንደር ሰው ከመሆናቸው አንጻር "በጎንደሬው" ባህልና ወግ ልማድ ተቀርጸው ያደጉ ከመሆናቸው አኳያ ፈሪሃ እግዚአብሔር፣ ትሕትና፣ ርኅሩኄ፣ እውነተኛና ሐቀኛ፣ ጀግና ሽማግሌ አክባሪ ለሕዝብ አዛኝና የሕዝብ ፍቅር የነበራቸው፣ እንዲሁም ሲጣሉና ሲቀጡ ምክንያታዊ እንደነበሩ የሚመስል በስንኙ መልእክትና ቃላት ላይ ይስተዋላል። ነገር ግን ሕዝቡ ተማሮ በሽሙጥ የሥርዓቱ አስተምህሮ ሻለቃ መላኩን ምን ያክል ካደጉበት ባህል ታሪክ ልማድ እንዳወጣቸው ማዘኑን በቃል ግጥሙ ዙሪያ ያነጋገርኳቸው ግለሰቦች አስረድተውኛል (ሽመልሰ ደምለው፣ዋኘው ዘዋለ፣የኔታ ተሾመ)። ሻለቃ መላኩን "አንድ መላኩ ነው" እያለ ከመላእክት ጋር በመመሰል በተቃራኒው "አብዮት ልጇን ትበላለች"፣ "ከሁሉም በፊት አብዮቱ!" የሚለው የተቀዳ ፍልስፍና ምን ያክል እንደተፈታተናቸው ለማሳየት ይሞክራል። አንዳንዶቹ በመላኩ ጊዜ ከሰባት ልጆቼ አንዱ ተርፎ አሜሪካ ሀገር በመሰደዱ አሁን አሳለፈልኝ የሚል ሽሙጥም አላቸው። በተለይ በሻለቃ መላኩ ዘመን ከ1969 ዓ.ም. ጀምሮ መብረቅ የተሰኘ ኮሚቴ በማቋቋም በክፍለ ሀገሩ የቀይሽብር ዘመቻ እንዲፋፋም ተደርጓል። ነገር ግን ነጭ ሽብር በማለት መጀመሪያ መጠፋፋቱን የጀመሩት ኢሕአፓዎች መሆናቸውን መገንዘብ ያሻል (ዝነከማሁ፣ Gebru, 2016)። ሆኖም ያብዮቱ ሞገድ መልካሙን ከመጥፎ የማይለይ ሆኖ እንጂ ሻለቃው አዛኝ፣ ትሑት፣ አዳማጭ፣ የማያዳሉ፣ ጀግና ወዳድ፣ የሌባ መድኃኒት፣ ሥራወዳድ፣ ሰው አክባሪ፣ ለጋስ፣ ቆራጥና የመፍተሄ ሰውም ነበሩ የሚሉ ሰውችም አጋጥመውኛል። ለምሳሌ፣ ወ/ሮ አቡኔ ስጦታው የተባሉ የጎንደር ነዋሪ እንደሚሉት "በኢሕአፓ አባልነት ተጠርጥራችኋል ተብለን አዳራሽ ውስጥ ገብተን ሰው ሁሉ ፈርቶ እኔንም ሰው በሹክሹክታ እንዳትናገሪ እየተባልኩ ተናገርሁ። "መለኩ ተፈራ የግዜር ታናሽ ወንድም፣ የዛሬን ይማሩን ከእንግህ አይለምድም" ብዬ ተናገርኩ። በዚሁ ንግግር ስትፈለጉ ትመጣለችሁ ተብለን ተለቀቅን። ተደሰትን። በዛው ከኔምጋር ተዋውቀን ባለቤቴ የልጄ አባት ወታደር ስለነበር ተጠፋፍተን ስለነበር አፈላልገው ተቆራጭ ተደረገልኝ በማለት ተናግረዋል። ልጅ ሳሉ በትምህርታቸው ጎበዝ ነበሩ ተጃንሀይ ተቆራጭ እየተደረገ ከሚማሩ ልዩ ተማሪዎች ውስጥም ነበሩ። ሸህ ኢብራሂም የተሰኙ የጎንደር ነዋሪም ሁለት ጊዜ ቶርቾ/ ተደብድቤያለሁ ይሕም የሆነው ከመሰል የክርስትና እምነት አባቶች ጋር በጋራ ምን እናድርግ ብለን ተመካክረን ሕዝብ አይለቅ በመለታችን የተነሳ ነበር ይላሉ። ነገር ግን ድብደባው የላይ ላይ ከገላ ላይ የሚቀር ነበር። የኢትዮጵያ እሴት አደጋውስጥ የገባ ቢመስልም አልጠፋምና ስንውጣ ስለአንድነታችን ስለወንድማማችነት ስለአብሮበታችን ነበር የሚወራው። ከዚሁ ጋር በተያያዘ ብዙ ጊዜ የማይነሳው ነገር ሻለቃ መላኩ ሥራ ወዳድ እውነትን ደፍሮ ለተናገረ የሚምሩ የሚሸልሙም ነበሩ በማለት ምስክርንት ይሰጣሉ። ወህኒ ቤት ተጠርጥረው ገብተው በቤቱ ባሳዩት የሥራ ተነሽሳሽነትና አርአያነት ከሞት የተረፉና በሰላም ከሥር ቤት ወጥተው የግል ሕይወታቸውን የኖሩም እንደ ነበሩ ይናገራሉ።

በ 4 ቁጥር የተመለከተው ግጥም ላይ የሚታየው ጭብጥ ሻለቃ መላኩን በማጋነን "ከመላእክት" ጋር ተነጻጽረው አንድ መላኩ

ነው በማለት ተሽሚጧል። ቅዱሳን መላእክት እንደሳቸው "የማይፈሩበት" እና የያንዳንዱ ሰው እስትንፋስ በእርሳቸው በጎ ፈቃድ ሥር መሆኑንና በከፍተኛ ልዕልና ተሰለው ሕዝቡ በርሳቸውና በሥርዓታቸው ተጽዕኖ ሥር እንደነበር የሚያሳየን እንደሆነ መታዘብ ይቻላል። ከዚህ ጋር ተያይዞ አባ እንድሪያስ ሊቀ ጳጳስ ዘጎንደርየሻለቃ መላኩ ዘመን በጸሎት መልክ "ከቀሳፊ መልአክት ይሰውረን'' በማለት ገልጸውታል። በጉዳዩም ተጠይቀው "ሰው ከመቼ ወዲህ መልአክ ይሆናል?" ሻለቃ መላኩ ሰው መሆኑን ነው የማውቀው። እኔ ያልኩት "አምላኬ በጎ ዘመን አምጣ!ነው( መረጃ ሰጪ፣ ሰሳይ ሳህሌ፣ ሽመልስ ደምለው)።ለሕዝብና ለሀገር የማይጠቅም አስተምህሮ፣ ሰው በጎ እንዳያስብ የሚያንሾካሽኩ መልአክት አሉና ከእነሱ ሰውረን" በማለት የሻለቃውን ዘመን ተችተዋል። አባ እንድሪያስ ጳጳስ ዘጎንደር በ1967 ዓ.ም. ተንሳዔ በዓልን ለማክበር ፈቃድ ለመጠየቅ ለውቅቱ የጎንደር ክ/ሀገር አስተዳዳሪ ክቡር አቶ በዛብህ ገብሬ የጻፉት ደብዳቤ የነበረውን የወቅቱን አለመረጋጋት የሃይማኖት፣የሕዝብና የመንግሥት ግንኙነት ምን ይመስል እንደነበር ያስረዳል። ፋይል /95 / ደብዳቤ ቁጥር 412/67 ቀን 24/8/1976 ዓ.ም። አንድ ሊታወስ የሚገባው ጉዳይ እኒህ የሃይማኖት አባቶች የዘመኑን መፈክር "ኢትዮጵያ ትቅደም"ን ብቻውን አብዛኛው ሰው እንደሚያደርገው አልተውትም ፈቃደ ፈጣሪን ጨምረውበታል። በዚህም መሠረት በሚጽፏቸው ደብዳቤዎች ላይ ያለምንም ማቅማማት "በእግዛብሔር ቸርነት ኢትዮጵያ ትቅደም" ፣"እግዚአብሔር የኢትዮጵያን እርምጃ ይባረክ "እያሉ ማሳረጊያ ይሰጡ ነበር፤ ለምሳሌ፣አባ እንድሪያስ ጳጳስ ዘጎንደር፣ ለጋይንት አውራጃ አስተዳደር ቤተክህነት ጽ/ቤት ግልባጭ ለጎንደር ክፍለ ሀገር አስተዳደር ጽ/ቤት ደብዳቤ ቁጥር 9164 ቀን 4/2/1969 ዓ.ምና አባ መርቆሪዎስ ጳጳስ ዘጎንደር፣ ለጎንደር ክፍለሀገር አውራጃ ቤተክህነት ጽ/ቤቶች ስለ ታሪካዊና ባህላዊ ቅርሶች ምዝገባ በተመለከት ለባህል ሚኒስቴር ልዑካን ትብብር ይደረግ ዘንድ የጻፉት ደብዳቤ ቁጥር 816/77 ቀን 16/6/77ዓ.ም መመልከት ይቻላል።

በሌላ በኩል ጋዜጠኛ ጳውሎስ ኞኞ ከሥራ ባልደረቦቹ ጋር ጎንደር ለሥራ መጥቶ ሻለቃ መላኩ ይቀበሉታል። ከዚያም ሻለቃው "ለመዝናናት ገንዘብ አሲይዘን ካራምቡላ እንጫወት" የሚል ሐሳብ ለጳውሎስ ያነሳሉ። ጳውሎስም "ያሸነፍኩህ እንደሆን ሽጉጥ ማውጣት የለም!... አንተ ቶሎ ወደ ሽጉጥ ትሄዳለህ" የሚል ቅድመ ሁኔታ እንዳስቀመጠና እባክህ ሰው አትግደል ብሎ በአሽሙር እንደተናገረ ደረጀ የተባሉ ጸሐፊ የጳውሎስ ኞኞ የሕይወት ታሪክ በተሰኘ መጽሐፋቸው አስነብበዋል።

በተራ ቁጥር 5 የተጠቀሰው ግጥምም መወድስ ይመስላል፤ ይሁን እንጂ የሻለቃውም ሆነ የመንግሥታቸው ርዕዮት እንከን አልባ እንዳልሆነና የሀገርን ተጨባጭ ሁኔታ ያገናዘበ የእድገት አቅጣጫ እንደተከተሉ በማስመሰል <u>እንደመላኩ ነው መሄድ መራመድ</u> እየተባለ ተሽሚጧል።

## 4.2.ማኅበራዊ ጉዳዮች[4]

### 6. የተማረ እሚወድ ትምህርትን ያስፋፋ፣ የደርግ ሥርዓት እያደር ይፋፋ፡፡

የሰውን ልጅ "አለማወቅ የሚበድለውን ያክል ማንም አይበድለውም" እንዲሉ ማኅበራዊ ኑሮን ለማጠናከር የጋራ ችግርን ለማስወገድ ለሀገርም ሆነ ለራስ እድገትና ብልጽግና ለማግኘት ትምህርት አይነተኛ መሳሪያ ስለመሆኑ ጥርጥር ያለው ጉዳይ አይደለም። ነገር ግን ምን ዓይነት ትምህርት ያስፈልገናል? እንዴት? መባልም ነበረበት። ከዚሁ ጋር በተያያዘ መስፍን ወልደማሪያም" ሀገርን ለማሳደግ ብቸኛውና አስፈላጊው ነገር ትምህርት ነው ብለው የድሆችን ልጆች ሁሉ አስተማሩን፣ በየፈረንጅ ሀገር ላኩን፣ 'ፈረንጅ' ሆነን ተመለስን። ያስተማሩንን ተምረን

4 እዚህ ላይ ማኅበራዊ ጉዳዮች ስንል ለመሠረተ ልማትና ሌሎችም የሕዝብ ኑሮ ማሻሻያ ሁነኛ መሳሪያ ናቸው የሚባሉትን እንደ ትምህርትና መሰል የልማት መንገዶችን ለመጠቆም ታስቦ ነው።

ተመለስን….።" (ወልደ ጊዮርጊስ፣ 1948፡1-2 ፤መስፍን፣2012፡24)በማለት በጃንሆይ ጊዜ ሳይቀር የነበረውን የትምህርት ሥርዓት ችግር ይገልጻሉ። በተጨማሪም ብርሃኑ ድንቄም ምዕራቡ ዓለም የተማሩ ኢትዮጵያዊያን ትምህርት እድል አግኝተው ሲሄዱ እንደሚባለው የተሻለ ነገር ይዘው መጥተው በራሳቸው ተማምነው የሕዝቡ ሁለንተናዊ ሕይወት በፍቅርና በእምነት አድጎ መልካም ምሳሌነቱን ለተከታዩ ትውልድ እንዲያስተላልፍ ከፍተኛ መሪነትን ያሳያሉ ቢባልም አለሆነም። ለምን? ለሚለው ምላሹ ቁሳዊነትን ብቻ መሠረት ያደረገ ትምህርት ተምረው ስለሚመጡ ነው የሚል ምላሽ ያስቀምጣሉ(ብርሃኑ፣2010)።ንጉሡ የስድስት ኪሎውን ገነተ ልዑል ቤተመንግሥታቸውን ከዩኒቨርሲቲ ኮሌጅነት ወደ ሙሉ ዩኒቨርሲቲነት ሲያድግ ከተናገሩት ንግግር እንደምንረዳው "….ይህ ዛሬ መርቀን የምንከፍተው ዩኒቨርሲቲ በኢትዮጵያ ታሪክና ባህል ላይ የተመሠረተና ኢትዮጵያ በረጅም ታሪኳ ያጠራቀመችውን ታሪክና የባህል ቅርስ በመመርመር ከዘመን አመጣሹ ዕውቀት ጋር በማስተሳሰር የወደፊቱን የኢትዮጵያ ሕዝብ ታሪክ አቅጣጫውንና የሚይዘውን ለመምራት የሚቻልበትን ዕውቀት የሚገበይበት የትምህርት አደባባይ ነው።" (ብሩክ፣2010፡229)፣ቢሉም በተግባር ግን እምብዛም አልታየም። ምክንያቱም መምህራን እንዲሁም ሥርዓተ ትምህርቱ ጭምር ከውጭ የተቀዳ ስለነበረ ነው። ጃንሆይም ለሚሲዎናዊያን አስተማሪዎችና ትምህርት ቤቶች ጓዳቸውን በእምነት ከፍተውላቸው በዘመናዊ ትምህርት ሰበብ የምዕራብን ርዕዮት ማራገፊያ እንደሆኑ የተረዱት አይመስልም። ውጤቱም እየቆዬ በተማሪዎቹ እየጎለመሰ ሲሄድ እየታየ መጣ ። የደርግ መንግሥትም ቢሆን ትምህርት ከብዝበዛ ነጻ መውጫ መሳሪያ ስለመሆኑና በሰፊው ሕዝብ ፍላጎት ላይ የተመሠረተ ዕውቀት መቅሰሚያ ነው ቢልም የተሳካለት አይመስልም። የማኅብረተሰባዊነት ርዕዮትም ብቸኛው የሀገርን የመልማት እድል ይወስናል የሚል እምነት የያዘ ነበር። አስተማሪዎቹም የዚሁ አስተሳሰብ ኣርዓያ መሆን እንዳለባቸው እንደ ግዴታ ይወሰድ ነበር። የወታደራዊው መንግሥት በመላ ሀገሪቱ ገጠር ከተማ ሳይል መሃይምነትን ለማጥፋት ከ1971 ዓ.ም. ጀምሮ በመሠርተ ትምህርት ዘመቻ ከፍተኛ ጥረት አድርጓል፤ ዓለም አቀፍ እውቅናም አግኝቶበታል።

ነገር ግን የመሠረተ ትምህርት መደላድል የተጀመረው አሁንም በጃንሆይ ጊዜ ስለመሆኑ መገንዘብ ያሻል። ትምህርትን በስፋት ለኢትዮጵያ ሕዝብ ለማዳረስ መሠረተ ትምህርትን ጨምሮ የደርግ መንግሥት ፕሮግራም እንደሆነ በስፋት ይነገራል። ነገር ግን በግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዘመን እቅዶቹ እንደወጡና በተግበርም መታየት የጀመሩበት ሁኔታም ነበር። ደርግ ያንን የለውጡ አካል አድረጎ እንደወሰደው መገንዘብ ይቻላል። ለምሳሌ፣ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃለሥላሴ ትምህርትን ለማስፋፋት በማሰብ በወቅቱ በተማሩ ኢትዮጵያዊያን በጎፈቃድ የተመሠረተ 'ብሔራዊ የፊደል ሠራዊት ማኅበርን' መመሥረት ምክንያት በማድረግ ሐምሌ. 14 1954 ዓ.ም የተናገሩት መልእክት መመልከቱ በቂ መረጃ ይሰጣል የሚል እምነት አለን። "የማንኛውም አገር ዕድገት ሊገፋና ሊፋጠን የሚችለው ሕዝብ በሙሉ መሠረታዊ ትምህርት ሲኖረውና በዚህ ሳቢያ የጠቅላላው የመንግሥት ዓላማ ገብቶት ተካፋይ ለመሆን ሲችል ነው። ትምህርት ለሕዝባችን ዕድገትና መሻሻል መድኅን መሆኑን ተረድተን በተቻለ መጠን ትምህርት ለመላው ሕዝባችን ለማዳረስ ደክመናል ውደፊትም እንደክማለን።….ሕዝባችን በሙሉ ማንበብና መጻፍ እንዲችልና ድንቁርና እንዲጠፋ ያለንን ምኞት እስከ ዛሬ ያቋቋምናቸው ትምህርት ቤቶች ብቻቸውን ከግብ ሊያደርሱት የማይችሉ መሆኑን በመረዳት በዕድሜው ወይም በሌላ ምክንያት ከነዚህ ትምህርት ቤቶች ገብቶ ለመማር ያልቻለው ሳይማር እንዳይቀር በማለት በተጨማሪ "የመሠረተ ትምህርት "ድረጅት እንዲቋቋም አዘዝን፣ በሥራ ላይም ይገኛል ብለው ተናገረዋል።" (ሁሉ ይማር የብሔራዊ የፊደል ሠራዊት ማኅበር…. ገጽ፣ 5)። ባንድወቅት ሊቀመንበር መንግሥቱ የመሠረተ ትምህርት ስኬት በአሃዛዊ መስፈርት ብቻ የሚለካ አይደለም። ለምሳሌ፣1966 ዓ.ም. 93% የነበረው ያልተማረው ብዙኀን ሕዝብ በ1976 ወደ 37% መውረዱን ተናገረው "በመሠረተ ትምህርት የተካተቱት የትምህርት ዓይነቶች የሠርቶ አደሩን ሕዝብ አመለካከት አስተሳሰብና አኗኗር ለመለወጥ የሚያስችሉ ሆነው ተቀርጸዋል። ዘመቻውም የባህል አብዮት አካል ከመሆኑ አንጻር ሠርቶ አደሩ ሕዝብ በአዲሱ ኅብረተሰብ ግንባታ ሂደት ውስጥ ሕይወቱን ለመለወጥ በሳይንስና ቴክኖሎጂ ውጤቶች በሚገባ ለመጠቀም የዕውቀት አድማሱ እየሰፋ መሄድም አለበት።"በማለት ንግግር አድርገው ነበር። (ብሔራዊ የመሠረተ ትምህርት ዘመቻ፣ 1977፡1-2)።

ሆኖም ግን ትምህርታዊ ዘመቻው ሀገራዊ አካሄድና መሠረት ስላልነበረው የተጠበቀውን ያህል በሕዝቡ ማኅበራዊ፣ ምጣኔ ሀብታዊ እና ፖለቲካዊ ኑሮ ላይ ያመጣው ለውጥ ይህ ነው የሚባል አልነበረም። የፊደል አንባቢ እንጂ የመጽሐፍ አንባቢዎችን ለማውጣትና ኑሮውና አእምሮው እንዲያድግ የተሠራ አይመስልም። ምናልባት ሰዎች ስማቸውን መጻፍ ችለው ካልሆነ በስተቀር። ባጠቃላይ የተሻለ ዕውቀትና ግንዛቤ የነበራቸው ሰዎች እያጠፉ እንደገና "ሀ" ተብሎ የተጀመረበት አግባብ በስፋት ይስተዋል ነበር። ይህም በየትኛውም ዘርፍ ሀገር ጎድቷል። ለሥርዓቱ ዋናው አንገብጋቢ ነገር ርዕዮቱን አለመቃወም ይመስላል። ከላይ እንደተባለው ይህ ባንድ ጊዜ ደርግ የፈጠረው ችግር አይመስልም። ደርግ ውስጥም ሆነ በተቀዋሚነት የቆሙት እርስ በርስ የተጠፋፉት ወገኖች የማንና የምን ውጤቶች ናቸው? የሚል መሠረታዊ ጥያቄ ሊነሳ ይገባዋል። ከዚሁ ጋር ተያይዞ በሀገራችን ታሪክ የዘመናዊ ትምህርትን የተቀበልንበት መንገድ በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ይህ ነው የሚባል ለውጥ እንዳይመጣ አድርጓል

የሚል እሳቤ አለ። ኢትዮጵያ የምትባለውን ጥንታዊት ሀገር የራሷ ልጆች ካባቶቻቸው ስለሀገራቸው ዕውቀት የሚገበዩባት ሳትሆን የውጭ ሀገር ባላንጣዎቿ በተለያየ ጊዜ እየተቀባበሉ አንድነቷንና ክብሯን የሚያጎድፍ ፍልስፍናቸው ባንድም ይሁን በሌላ በሀገሪቱ የትምህርት ገበታ ሳይቀር ልዕልና እየያዘ እንዲመጣ የምዕራባዊ የትምህርት ሥርዓት አስተዋዕኦው ከፍተኛ ይመስላል። ይህም የሀገሪቱን የነጻነት ታሪክና ባህል በእጅጉ የተፈታተነ እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል። ለዚህም ብዙ ምክንያቶች ከዘርፉ ባለሙያዎችና ከሕዝቡ ሲነሳ ይስተዋላል። እንደመነሻ የሚሆን የትምህርት ባህል ያላት ሀገር ምንም እንደሌላት በሁሉም ነገር የውጭ እውቀት ተቀባይ ለመሆን እንድትዘጋጅ መደረጉ አግባብ አልነበረም።ሆኖም በመርሕ ደረጃ በሚመስል መልኩ ሌ/ኮሎኔል አጥናፉ አባተ የደርግ ምክትል ሊቀመንበር በንግግራቸው የሀገርን ታሪክና ባህል ለፖሊሲ ግብዓትነት መጠቀም የአማራጭ ጉዳይ እንዳልሆነ ባንድ ወቅት ተናግረው ነበር፤

> አብዮቱን በሥራ ላይ ለማዋልና ግቡን ለመምታት የመንግሥትን ፖሊሲና ሥርዓት ተከትሎ በኢትዮጵያዊያን ባሕልና አኗኗር መሠረት መካሄድ ይኖርበታል። የኢትዮጵያ ሕዝብ ባህሉ እንዲከበርለት ክብሩ እንዲጠበቅለት የሚፈልግ ታላቅ ባለታሪክ በመሆኑ፣ የሚደረገው የለውጥ ንቅናቄ ሁሉ ኢትዮጵያዊነትን የያዘ መሆን ይኖርበታል። .... ለውጡንም ራሱ ያመጣው እንጂ የወጭ እጅ የሌለበት የራሱን ለውጥ ፈልጎ የጀመረ አሁንም በራሱ ባህልና ዕውቀት የሚመራ ሕዝብ መሆኑ መታወቅ ይኖርበታል

(በክቡር ኮሎኔል አጥናፉ አባተ የተጻፈ ደብዳቤ ቁጥር አ/ድ/ 3/2//8/11/1254 ፣ ቀን ነሐሴ 20 1967 ዓ.ም ፣ገጽ፣ 2-3)።

ነገር ግን ከንግግር ያለፈ ደርግ ይህን መሠረታዊ ጉዳይ በተከታታይ ሥራዎቹ ላይ በተግባር ሲያሳይ አልታየም። እንዳውም በተቃራኒው እንደሄደ መገንዘብ ይቻላል። ሕዝቡ ያካበተውን ማኅበራዊ፣ ባህላዊና ፖለቲካዊ አስተሳሰብ በጅምላ "ኋላ ቀር" በማለት ሥርነቀል ለውጥ በሚል አስተሳሰብ የጫነ እንጂ ነባራዊ ሁኔታዎችን ያገናዘበ እንዳልነበረ ማየት ይቻላል (ቃል መረጃ ሰጪ፣ እማሆይ ራዱ ብዙነህ፣ የቃል መረጃ የሰጡበት ቀን 21/2/2005 ዓ.ም.፤ ሼህ እንድሪስ ሰይድ፣ ሼህ መሀመድ ሳኒ 14/ 3/2005 እና 14/3/2006 ዓ.ም)። ለምሳሌ፤ ምክትል ሊቀመንበሩ ከላይ እንዳሉት ኢትዮጵያ ረጅም እድሜ ያስቆጠሩ ሀገረሰባዊና ሃይማኖታዊ ዕውቀቶች ውጤት የሆኑ በርካታ ጽሑፍ ላይ የሰፈሩና ያልሰፈሩ ቅርሶች እንዳሏት ይታወቃል። በየገዳማቱና አድባራቱ፣ እንዲሁም በአብያተ መስጊዶች የምዕራባዊያንንም ሆነ የቀረውን ዓለም ቀልብ የሚስቡ በርካታ "የምርምር" ውጤቶችም ይገኛሉ። በተጨማሪም በማኅበረሰቡ ውስጥ በቀጥታ ያልተጻፉ ሕዝቡ የሚመራባቸው በርካታ የዕውቀት ውርሶች ከትውልድ ትውልድ እየተላለፉ የማንነቱ መገለጫ ሆነው ቆይተዋል። እነዚህን መመርመር እንዳስፈላጊነቱ ለእድገት ማዋል ጠቀሜታው የሚያጠራጥር አልነበረም። ሆኖም ደርግ "ዐይናችሁን" ላፈር የሚል መመሪያና ሕግ ያወጣባቸው ነበር። በተለይ አብያተ እምነቶች አካባቢ። ለመጥቀስ ያክል የቤተክህነት መድኀኒትና ሕክምና ዐዋቂዎች ሌሎች ሀገረሰባዊ ባለሙያዎችን ማስታወሱ እንደሚበቃ የዚህ ጥናት ተሳታፊዎች በጥልቀት ያብራሩታል (ቃለመጠይቅ ከአቶ መርድ ዳምጤ፣ አቶ አላምረው ላቀውእና እማሆይ ራዱ ጋር 5/6/2006 ዓ.ም.)።

ከዚህ ጋር ተያይዞ ግጥም 6 ላይ እንደቀረበው ''የተማረ እሚወድ'' የሚለው ምናልባት ጥሩ ፅንሰሐሳብ የያዘ እንደሆነ የጥናቱ ተሳታፊዎች በስፋት ይገልጻሉ (መረጃ ሰጪ፣ሲሳይ ፣ዋኘው፣ 2006)። ይህም ሲባል ደርግ "የተማረን ሰው" አቅጣጫ ወይም አስተያየት የሚቀበል ሥርዓት አለመሆኑን ለማስረዳትና አምባገነናዊ ተምሳሌትነቱን ለማሳየት ሳይሆን እንዳልቀረ መረዳት ይቻላል። በተጨማሪም ሥርዓቱ "ከተማረው" ማኅበረሰብ ጋር የነበረው ግንኙነት ባብዛኛው ሆድና ጀርባ እንደነበር ይጠቁማል (ዝነከማሁ፣ዘላለም ወላይ የቃል መረጃ የሰጡበት ቀን 8/2/2005 ዓ.ም.፤ በተጨማሪ የብሔራዊ መሠረተትምህርት አስተባባሪ ኮሚቴ ፣1982 ዓ.ም)። ባብዛኛው እንደምንለው ትውልዱ ሥር ነቀል እያለ ሀገራዊ ፍልስፍናን ንቋል፤ ሀገር በነጻነት ያቆዩትን አባቶችን አዋርዷል። ስለሆነም ተማርን የሚሉት የደርግ ካድሬዎችም ሆኑ ከነሱ ውጭ የነበሩት የተማሩ ናቸው የሚባሉት የባእድ ርዕዮት በስሜት ተሸካሚ በመሆናቸው ግራ መጋባትና ቶሎ ቶሎ መመሪያዎች እየወጡ ሕዝብ አደናጋሪው የበዛበት ጊዜ ነበር። በተያያዘም (Tekeste,2008:1-21). የሚከተለውን ሐሳብ ጽፈዋል። "... another fact to note

is that in addition to the racist description and analysis of Ethiopian civilization mostly from out side , the most tenacious enemies of Ethiopian culture and civilization are its sons and daughters who are the product of the modern education system…" . በተጨማሪም ፕ/ር መስፍን ወ/ማሪያም" …አድዋ ላይ የጣሊያንን ጦር ድባቅ የመታው የአውሮፓ ምሩቅ አልነበረም፤ የኢትዮጵያ "ትምህርት" ምሩቅ እንጂ።…. የአስኳላ ትምህርት ማንነትን እያሳጣ የፈረንጅ አንብዳጅ አደረገን። ራሳችንን ወደ መናቅ መጣን። የሚበልጡንን በተጠና ዘዴ ክፍተታችንን ሞልተን ልዩነታችንን ለማጥብብ ጥረት አላደረግንም ……። ታሪካችንም ሃይማኖታችንም ኋላቀር ተባለ….።" መስፍን፣ ገጽ፣ 128፤ኃይለ ገብሬል፣2007 ዓ.ም)።

ኅዳር 1967 ዓ.ም. ተማሪዎቹ በጭፍን "ኢትዮጵያ የምትመራው በሶሻሊዝም ካልሆነ በስተቀር ለዕድገት በኅብረት ዘመቻ አንሳተፍም . ." በማለታቸው የመንግሥትን ትኩረት እንዲስብ አስገድደዋል። ግልጽም ሆኖ ይሁን ሳይሆን ሶሻሊዝም በወቅቱ የሁሉንም ቀልብ የገዛ የዘመኑ እንቁ አስተሳሰብ ነበር። ጥያቄውንም የደርግ መንግሥት ብዙም ሳይመክርበት ተቀብሎታል (ፍቅረሥላሴ፣ 2006 እና ፋሲካው፣ 2014)። ስለሆነም የተደበላለቀና ያልጠራ አቅጣጫ ውስጥ የነበረ መንግሥት እንደነበር እንረዳለን። ሳይንሳዊ ኅበረተሰባዊነት እንደፍልስፍና ችግር እንደሌለበት ብዙዎች ሀሳባቸውን ያቀርባሉ። ችግሩ ተማሪዎቹ፣ የዘመኑ ምሁርም ሆኑ የደርግ አባላት አልገባቸውም፤ የመመራመሪያ ጊዜም አልነበራቸውም። ለምሳሌ፤ ተማሪዎቹ ለትግላቸው አርዓያ ያደረጉት የእነቸጉቬራ፣ ማኦ፣ ካስትሮ ገድሎችን ነበር (ፋሲካው፣ 2014)። የግጥሙ ውስጠ ትርጉምም የደርግ ሥርዓትን በማግዘፍ ሥርዓቱ ያመጣው ለውጥ እምብዛም እንደሆነ ይተቻል። የሕዝቡ ነባር ሥነምግባራት ዕውቀት በአዲስ ተለውጠው መልካም የማይባሉ ሥነሰብዓዊ እና ሥነልቦናዊ ግድፈቶች በስፋት ይታያሉ በማለት ይወቅሳል። ለምሳሌ፤"የደጅ ጸበል የቆዳ መንከሪያ ይሆናል" እንዲሉ የራስን ባህልና ዕውቀት ማጥላላት፣ ለመጤው ከፍ ያለ ቦታ መስጠትን ያጠቃልላል። አንድ የደርግ ዘመን ሰነድ የኢትዮጵያን ረጅም ታሪክና ባህል በጠቅላላው በሚከተለው መልኩ ከአብዮቱ ጋር በማነጻጸር ይገልጸዋል። "የአብዮታችን ዓላማ ሦስት ሽህ ዘመን በነጻነት ሥም እየተሸነገለ ለጭቆና፣ ለብዝበዛና ለተዛባ ፍርድ ተዳርጎ የኖረውን ጭቁን ሰፊ ሕዝብ እውነተኛ ነፃነት እኩልነትና ፍትሕን በማስጨበጥ የጋራ አለኝታ የሆነችውን ሕዝባዊት ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን መሥርቶ … ራሱን በራሱ እንዲመራ፣ ብሎም እንዲያስተዳድርና በጋራ ሀብት ላይ ሥልጣን ኖሮት ራሱን እንዲችል ነው ……" (የመደብ ትግል፣ 1981፡ 6) በማለት የረጅሙን የሀገሪቱን ታሪክና ባህል እሚያስተምረን ጥቂት ወይም ምንም እንደሆነ በድፍረት ይናገራል፡፡ ይህ አካሄድ አግባብ አይመስልም። የህገረሰብ ዕውቀት ተመርምሮ የሚጠቅመው እንዲቀጥል መሻሻል ያለበት እንዲሻሻል በለውጡ ከቀድሞው በተሻለ ሊጠበቅ ሊበረታታ ሲገባው ጭራሹን እንዲተውና የዕውቀቱ ባለቤቶች እንዲሸማቀቁ ተደርጓል። በቅድመ አብዮት ኢትዮጵያ የነበረውን የትምህርት ሥርዓት በተለይ ሀገራዊ መልካም እሴቶችን የሚያጎለብቱ ሥራዎች ከሥርዓቱ ጋር እንዲወገዱ የተደረጉ በሚመስል መልኩ በየትኛውም የትምህርት ደረጃ የሚሰጡት የትምህርት ዓይነቶች ስለዘመኑ የመንግሥት ርዕዮት ዓለም እንጂ ስለነባሩ የኢትዮጵያ ባህል ትልቅነትና አዎንታዊ ልዕልና ላይ የተመረኮዙ አልነበሩም (አጋፋሪ አበበ አየለ እና አቶ ሽመልስ ደምለው የቃል መረጃ 6-7/4/2006 ዓ.ም፤ Setargew Kenaw, 2005)፡፡ ማኅተመሥላሴ ስለ ኢትዮጵያ ሕዝብ ሁለንተናዊ መልካም ባህና ታሪክ ሲናገሩ፤"…. . ኢትዮጵያዊ በቂና በሠረተ ጠንካራ የሆኑ የመንፈስ ቅርሶች ስላሉት ከነዚህ እየወጣና እየራቀ ካልሄደ በቀር ማንኛውም መልካም ዕድል ሊለየው ስለማይችል ነው" (ማኅተመሥላሴ፣ 2007፡11-12) በማለት፣ "ነገር ከሥሩ ውሃ ከጥሩ" እንዲሉ ከተመረመረ የሚያስተምር ወደፊት የሚያራምድ መልካም ባህል እንዳለን ማስገንዘቢያ ሰጥተዋል። እዚህ ላይ ብርሃኑ ድንቄ ታሪክንና ባህልን ባግባቡ የማወቅ የመረዳትና የመተንተን ጥቅሙን በሚከተለው ግጥም ይጠቁሙናል። ከየት እንደ መጣ የማያወቅ ትውልድ፣ እንዴት ሊያውቅ ይችላል ወዴ[የ]ት እንደሚሄድ (ብርሃኑ፣2010.41)። በተጨማሪም አንድ አባት በአብዮቱ ማግስት ሁኔታዎችን በማየት ምክር አዘል መልእክት

ነሐሴ 10 ቀን 1970 ዓ.ም. ለደርግ አባልና የጎንደር ክፍለሀገር ዋና አስተዳዳሪ ለነበሩት ሻለቃ መላኩ ተፈራ የጻፋት፣ "ታሪክን ማወቅ" ብለው የፃፉት ለሀገር ግንባታ ጠቀሜታው ምን ያህል ትልቅ እንደሆነ በሚከተለው መልኩ አትተዋል፤

ታሪክ የተማረ መርማሪ ጠያቂ ፣
የልጅ ሽማግሌ ይሆናል ዐዋቂ፣
የግድ የሚገባ እንድትማሩት ፣
ያገሩን ታሪክ ነው የውስጡን ብልጎት፣
የቁመቱን መርዘም የወርዱን ስፋት፣
ንግድና ባህሉን የሰውን ዓይነት፣
ትምህርት ሃማኖቱን የቋንቋውን ስልት፣
ይህን ባትማሩ ልኩን ባታውቁት ፣
አሳፋሪ ነገር ይሆናል በውነት።
ይህን ሳይማሩ ያገርን ነገር፣
በሰው ሀገር ቋንቋ የሚነጋገር፣
አይመሰገንም ተብሎ ምሁር።
ይህን ለማስረዳት ምንድን ያስጨንቃል፣
የሽማግሌዎች ምሳሌ ይበቃል፣
አባቱን የማያውቅ አያት ይናፍቃል
(ጎንደር ክፍለ ሀገር ቤተ መዛግብት የተገኘ ግጥም፣. 1970 ዓ.ም)።

በማለት የቋጠሩት ስንኝ ኢትዮጵያ ውስጥ ያሉትን የሀገር በቀል ዕውቀቶች ያፈራቸውን አርቆ አሳቢ አባቶች ብስለት ይነግረናል፡፡ በተጨማሪም ትውልድና የታሪክ ቅብብሎሽ እንደተፋለሰና የሀገሪቱን ሁነኛ ችግር ለመጠቆም ሞክረዋል። የሀገሪቱ ሁነኛ በሽታ ተለይቶ ሁነኛ መድኀኒት እንዳልተገኘለት ለመግለጽም አስበው እንደጻፉት ተብራርቷል። ከዚሁ ጉዳይ ጋር ተያይዞ አንድ የወቅቱ ሪፖርት የታሪክንና ባህል መጣረስ በሚከተለው መልኩ ያስረዳናል። በአዲሱ የኅብረተሰብ ግንባታ ሂደት ሕዝቡን ወደ መደብ ትግሉ ለማምጣት ፈታኝ ከሚያደርጉት ጉዳዮች አንዱ የኢትዮጵያ ሕዝብ በተለይ አልተማረም የሚባለው የገጠሩ ገበሬ የጠንካራ የስነልቦና ባለቤት መሆኑ አንዳንድ የደርግ ካድሬዎች የተረዱት ይመስላል። ለምሳሌ፤ የጎንደር ክፍለ ሀገርን ሕዝብ ሲገልጹት፣ ሕዝቡ ስለሚነገረው ጉዳይ የአስተማሪውን ማንነት ባነጋገሩ፣ በቃላት አመራረጡ፣ በሃይማኖቱ፣ በሙያው፣ በእድሜው፣ ባለባበሱ እና በመሳሰሉት ሰውን የሚገምት ስለመሆኑ ይናገራሉ (የጎንደር ክፍለ ሀገር "ኢትዮጵያ ትቅደም" ሪፖርት፣ 1969 ዓ.ም)። በተጨማሪም "ይህ ጎንደር ክፍለሀገር በአስተዳደር ተረግጦ ተጨቁኖ ከመኖሩ የተነሳ ማንም የነገረውን የሚሰማ፣ የሚጠቅመውን ካማይጠቅመው የመለየት ችሎታ የሌለው ... በአስቸጋሪ ባህል ተጠምዶ የሚኖር የዋህ ሕዝብ ነው (ዝነከማሁ)። በማለት ሲገልጹትም ይስተዋላል። ይህ ለካድሬዎቹ የማርክሲዝምን ርዕዮት ያልያዘ ወይ በቶሎ አዎን ያላለ ፣እንደሰው አልቆጠሩትም፣ የሕዝቡ አስተዋይነት አርቆ አሳቢነትን አልተረዱትም፣ እንዴት እንደሚግባቡም አላሰቡም፣ ቢያስቡም አልቻሉም። በጠቅላላው ይህ አጋጣሚ የሚያሳየን ኅብረተሰቡና ደርግ፣ እንዲሁም ሌሎች የአብዮት ኃይል ነን ከሚሉ ወገኖች ጋር የነበረውን የታሪክና ባህል መጣረስ፣ ያለመግባባት መስተጋብር ፍንትው አድርጎ የሚየሳየን ነው።በተመሳሳይ (ሽፈራው፣ 2006፡ Viii) ይህንኑ የነባሩንናየአዲሱ ዕውቀት የመመሳጠር አስፈላጊነት ከታሪክ አረዳድ አንጻር ሲገልጹት "ታሪክ የለውጥና የቀጣይነት ኀብር ነው። ሙሉ በሙሉእንዳለ የሚቆይ ነገር የለም፤ሙሉ በሙሉ የሚለወጥም እንዲሁ። በነበረው መሠረት ላይ አዲሱ ሲገነባ የቀድሞውን እሴትና የአዲሱን ክስተት በማቀናበር ኅብረተሰባዊ እድገትን ማምጣት ይቻላል" በማለት የውኅደትን ጥቅም ያስረዳሉ።ፍቃደ አዘዘ በበኩላቸው በደርግ ጊዜ የነበረው የትምህርት ሥርዓቱ ብዙ ጉድለት እንደነበረበት ሲገልጹ፤

> የጊዜውን አስተሳሰብ ለውጥ በመከተል ተመዝኖ ለዘመኑ በሚጠቅም መንገድ ተዘጋጅቶ መቅረብ ይገባው የነበረው ምግባርና የልዩ ልዩ እሴቶችና ሥነሥርዓቶች ትምህርት ከዕለታዊ ኑሮ ጋር ባልተገናኙ ጽሑፎችና ዲስኩሮች በመተካቱ ብዙ

የእሴት፣ የምግባርና የየዕለት ኑሮ ሥነሥርዓት መቃወስን በአጠቃላይ በማኅበረሰቡ ላይ በተለይም በወጣቱ ላይ አመጣ (ፈቃደ፣1998 ፡154-155)።

በተጨማሪም የሰው ልጅ የመብት ጉዳዩን ሊያነሳበት የማይችል ሥርዓት መሆኑንና በዘመኑ የሚሰጠው ትምህርትም የሕይወት ለውጥ አላመጣም በማለት ለመግለጽ የታለመ ግጥም ሳይሆን አልቀረም። ለትምህርት እድሜ ገደብ ሳይደረግበት በሃገሪቱ በመሠረተ ትምህርት በሰፊው እንዲዳረስ ተደርጓል። ነገር ግን ትምህርቱ ያመጣው ለውጥ ከጣት ከመፈረም ወደ ብዕር ፊርማና ስም መጻፍ ያልዘለለ ለውጥ ነበር (ዝነከማሁ፤ እማሆይ ራዱ ብዙነህ፤ ሸህ እንድሪስ ሰይድ፣ ሸህ መሀመድ ሳኒ)። ትምህርቱም በታሪክ የሚታወቀውን የሀገሪቱን የሞራል ብርታትና የእምነት ጽናት ከነበረበት ደረጃ ቀጣይነት እንዲኖረው የተሠራው ሥራ አናሳ በመሆኑ የወገንተኝነት፣ ሸፍጥ፣ ማታለል፣ አድርባይነትና ምቀኝነት እየተስፋፋ እንዲሄድ መሠረት ሆኗል (ክንፈ ገብርኤል፣ 2012 ዓ.ም)። ስለሆነም በመሠረታዊነት ሊፈቱ የሚገባቸው ጉዳዮች አልተፈቱም የሚል እንድምታ አለው (ዝነከማሁ፤ እማኾይ ፀጋና አቶ ዋኘው ማለደ 51/4/2006 ዓ.ም)።

## 7. ለኛስ እግዜር አለን ይብላኝ ለሌላቸው፣ አቤት እያልን ነው መልስ እንዲሰጣቸው፡፡

እንደ ፍቅረሥላሴ ወግደረስ አገላለጽ፣ የኢትዮጵያ ሶሻሊዝም የታወጀው ታኅሳስ 11 ቀን 1967 ዓ.ም. ሲሆን፣ ከአፍሪካ ሶሻሊዝም ጋር ተመሳሳይነት እንዳለውና የታንዛኒያን ሶሻሊዝም እንደ ሠርቶ ማሳያ አድርጎ የተቀረጸ እንደሆነ ይገልጻሉ። ሥሙም የኢትዮጵያ ኅብረተሰባዊነት ወይም የኢትዮጵያ ሶሻሊዝም (ኢትዮጵያ ትቅደም) ይባል እንደነበር ይነገራል። በተለይ መጀመሪያ አካባቢ ሶሻሊዝም ማለት ለደርግ አባላት ግልጽ ስላልነበር "ኢትዮጵያ ትቅደም" እንደማለት ነው የሚል እሳቤም ተይዞ ነበር (ፍቅረሥላሴ፣2006)። በ1978 ዓ.ም በተጻፈ የማርክሲዝምና ሌኒኒዝም መዝገበ ቃል በተሰኘ መጽሐፍ ውስጥ የአፍሪካ ሶሻሊዝም በሚል ርዕስ እንደተብራራው ሶሻሊዝም በይዘቱ ዓለማቀፋዊ እንደሆነና ንድፈ ሐሳባዊ መመሪያውም ማርክሲዝም ሌኒኒዝም ነው ይላል (የማርክሲዝምናሌኒኒዝም፣1978)። በመቀጠልም ከዚህ ቀኖና ውጭ የተገነባ ሶሻሊዝም በተግባር ስኬት እንደሌለው ይመክራል። ሆኖም የአፍሪካ ሶሻሊዝም በትክክል የማርክስንና የሌኒን አስተምህሮ የተገበረ እንዳልሆነ ያመለክታል፡ ፡ በዚህም የተነሣ ውጤታማ ሶሻሊዝምን መገንባት አልተቻለም ይላል። ይህም የሆነው በልማዳዊ አሠራሮችና እምነቶች ሕዝቡ የተተበተበ መሆኑን ያስረዳል። በእንደዚህ አይነት የታሪክ እይታዎችና ትንታኔዎች የተጠመዱ በሥም ኮሚኒስት ለመሆን ካላቸው ጉጉት የተነሳ በራሳቸው ባህልና ታሪክ ላይ ጥላቻና ንቀት እንደነበረባቸው ከተግባራቸው መረዳት ይቻላል። በተመሳሳይ መስከረም፤ 1981 ዓ.ም. የተጻፈ ማርክሳዊ ሌኒናዊ የርዕዮት ዓለም መጽሔትም ለነጻነትና ለዴሞክራሲ አማራጭ የሌለው መስመር ሶሻሊዝም ነው ይላል። ይህ አስተሳሰብ ከሀገር በቀል ዕወቀትና አስተምህሮ ይልቅ ወደ ማርክሲዝምና ሌኒኒዝም አስተምህሮ ያጋደለ መሆኑ ግልጽ ነው (መረጃ ሰጪዎች፣ አጋፋሪ አበበ አየለ፣ ይርጋ ግርማይ ፣ እማሆይ ራዱ ብዙነህ፤ ፍሰሐ፣ 2008፤ ኃይሌ፣ 1969 ዓ.ም.፤ Semeneh Ayalew and Binyam Sisay,2013 )። በዚህም ሁለቱን አስተሳሰቦች አዛምዶ ለመሄድ ጥረት አልነበረም ለማለት የሚቻል ይመስላል። በኢትዮጵያም የነበረው የዘመኑ አስተሳሰብ ከዚህ የተለየ አልነበረም። ብዙ ሥርነቀል ማኅበራዊ ምስቅልቅሎችንም እንዳመጣ እንረዳለን (ዝነከማሁ)።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ርዕዮት ዓለም በጸሎተ ሃይማኖትላይ የተመሠረተ ሆኖ በአንድም ይሁን በሌላ የአብርሃም ሃይማኖቶች በሚባሉት በይሁዲ፣ በክርስትናና በእስልምና ቀኖና አስተምህሮ ለምዕተ ዓመታት የተዋረሰ ነው (መረጃ ሰጭ፣ አሰበ ነጋሽና ባዩህ በዛብህ፣ 2007)። ከእነርሱ በፊትም ከነበሩት ሀገር በቀል እምነቶችና ሰብዓዊ አስተሳሰቦች የተወሰዱት እሴቶች በርከት ያሉ ናቸው። ለምሳሌ ያክል፤ በሦስቱም ዓለማቀፋዊ እምነቶች ሃይማኖትና ሥነምግባር የሚለያዩ አይደሉም። በደርግና በትውልዱ ሥር ነቀል

ርዕዮት ምክንያት መልካም ሃማኖታዊና ባህላዊ እሴቶችና ተቋማት እንዲመነምኑ መደረጋቸው አግባብ አልነበረም። ከዚሁ ጋር በተያያዘ ሥርዓቱ የጎደለውን ነገር ግጥሙ የሚጠቁም ይመስላል። በግጥም 8 ላይ “እኛስ እግዜር አለን ይብላኝ ለሌላቸው” የሚለው ስንኝ እምነትና ጸሎት፣ እንዲሁም ምርቃትና እርግማን ትልቅ ቦታ ለሚሰጥባት ሀገር ቦታ እንዳይኖረው በመሠራቱና የሃይማኖት እሴትነትን በመዘንጋቱ ሕዝቡ የነበረውን ስሜት ያሳየናል። የደርግ ባለሥልጣናት “ሃይማኖት የላቸውም”፤ ሃይማኖት ቢኖራቸው ኑሮ እንዲህ ግፍ አይሰሩብንም ነበር የሚልና ሕዝቡ ግን በእምነቱ ጸንቶ እንዳለና አንድ ቀን ፈጣሪ ጩኸታችንን ይሰማንና መፍትሔ ይመጣል የሚል መልዕክት የያዘ እንደሆነ ከጥናቱ ተሳታፊዎች ማብራሪያ መረዳት ይቻላል (መረጃ ሰጪዎች፣ አቶ ዘላለም ወላይ ፣ ሲሳይ ሳህሌ፣ ዋኘው ዘዋለ፤ ደረጀ ትዕዛዙ፣ 2006 ዓ.ም፤ ብርሃኑ አስረስ፣ 2005 ዓ.ም)። በተቃራኒው ፍቅረሥላሴ ወግደርስ እኛና አብዮቱ . . በተሰኘ መጽሐፋቸው ገጽ፣207 ላይ ደርግ ከሃይማኖት አባቶችም ጋር ሆነ ከመዕመኑ ሃይማኖትን በተመለከተ ችግር እንዳልነበት በስፋት ገልጸዋል። ከዚሁ ጋር በተያያዘ ሻለቃ መላኩ ጋር ለፍርድ የቀረቡት አቶ ብርሃኑ አስረስ “...ከአፋኝ ቡድን ብቻ በቀረበ የጥፋተኝነት ሪፖርት ወደ ፍርድ ከመሄድ እኔንም አዳምጠኝ ብለው” ቢጠይቁ እድሉ ሳይሰጣቸው በድፍረት የሚከተለውን ተናግረዋል። ዳኝነት የሚሰጠው ግራ ቀኙን አዳምጦ ነው፣ በማለት “እኔ እምናገረው የሰው ቋንቋ ነው የመላእክት ቋንቋ አልናገርም ” በማለት ሻለቃውን አሸሟጠውባቸዋል። የጊዜውንም አስቸጋሪነት በምሬት ተናግረዋል.... (ብርሃኑ አስረስ፣2005 ገጽ ፣411-412።

ከዚሁ ጋር ተያይዞ ሕዝቡ በግጥሙ መሪዎቹን ነገር አትብሉ፣ እኔ ብቻም አትበሉ፣ ተባበሩ፣ ሁልጊዜ ጦርነት ያውም ከወገን ጋር ለማንም አይጠቅም፤ ውድቀትና መሳቂያ መሳለቂ ያደርጋል፤ ልበሰፊና ለሀገር አስቡ እባካችሁ ለማለት ይመስላል (ወርቁ ማለደ፣ አሰበነጋሽ)። በተጨማሪም፣ በወቅቱ በሚወጡት የመገናኛ ብዙሃን ጋዜጦች ጭምር ትኩረት ተሰጥቶ ይሠራበት የነበረው ጉዳይ “አብዮቱና ጠላቶቹ” በጅምላ ከአስተማሪነት ይልቅ ማስፈራራትንና ማን አለብኝነትን በዋናነት ማእከል ያደረጉ በመሆናቸው በዚህ ሁኔታ የተማረሩ ግለስብ በ1970 ዓ.ም. የሠርቶ አደር ልሳን ጋዜጣ ጎንደር ከተማ አራዳ አካባቢ ምረቃ ፕሮግራም ላይ ተገኝተው ወሽኔ (ጥሩ) ነው፤ ጎበዝ ከዚህ በኋላ ጋዜጣውን እተሙት፤ ነገር ግን አትሙበት እንዳሉ የመረጃ ሰጪዎች ትንተና ያስረዳል (መረጃ ሰጪዎች፣ አቶ እሸቴ ስሌማን ፣አቶ ይበይን ወ/ብርሃን እና ወ/ሮ ሙሉ አለሙ)። በተመሳሳይ ጊዜ ግራዝማች ዓለማየሁ የተባሉ ግለሰብ ተገርፈው (ቶርች ተደርገው) ሆስፒታል ተኝተው ሰው ሊጠይቃቸው ሂዶ “ምን ነካዎ?” ተብለው ሲጠየቁ፣ “ገረፍ አርጎኝ” የሚል ምላሽ ሰጡ ይባላል። ይህ አገላለጽ በሀገሬው ሰው ሁለት ትርጉም እንዳለው እንረዳለን፡ ፡ የመጀመሪያውና ግልጹ፣ ሰው ሆስፒታል የሚገባው ታሞ ነውና የገረፍታ ሕመም የተለመደ ነው። በሌሎች የሀገሪቱ አካባቢዎች ምች ይባላል። ቀላል ነው ተብሎ የሚተው አይደለም ፤ ከዚህ ሐሳብ ስንመጣ ግን ውስጠ ታዋቂ ትርጉም ያለው ጉዳይ አለ። ይኸውም ሰውየው በምጸት ምች ወይም ገረፍታ እንዳመማቸው በማስመሰል ተገርፈውና ተደብድበው እንደተኙ መረዳት ይቻላል (ዝኒከማሁ)።

**8. ቤቱ ለምን ይፍረስ የበላንበቱ የጠጣንበቱ፣**
**አልጋው ይፍረስ እንጂ ትኋን ያለበቱ፡፡ (ሽመልስ ደምለው)፡፡**

ሕዝቡ በጊዜው በዚህ ግጥም የሥርዓቱን ስሕተቶች አንጥረው አይተዋል። በመጀመሪያው ስንኝ ለፍተው ከሚመቻቸው ቦታ ላይ የሠሩት ቤት መፍረሱና ወደሌላ መሄዱ በእጅጉ አሳዛኝ እንደሆነ ሲገልጹ፣ በሁለተኛው ስንኝ ደግሞ አልጋው (የመንግሥት መንበረ ሥልጣን) ይፍረስ እንጂ ትኋን ያለበቱ በማለት የሥርዓቱን መበላሸትና ችግሮቹ የገዘፉ መሆናቸውን አምረው ተችተዋል። ለሥርዓቱም ውድቀትና በሕዝብ ዘንድ ጥላቻ እየበዛ የመጣው ያለሕዝብ ፈቃድ፣ ባለሙያ ባለተሳተፈበት በሊቀመንበር መንግሥቱ ኃይለማሪያምና በቅርብ ሰዎቻቸው ምክክር የተፈጸመ እንደነበር ይገለጻል።ስለሆነም የሰፈራው ትግበራ የአካባቢ ጥናት ባለሙያ፣ የሥነሰብዕ ዘርፍ ባለሙያ፣ የምጣኔ ሀብት ባለሙያ፣ የግብርና ባለሙያ፣ የእንስሳት እርባታ ባለሙያ እና የሌሎችንም ውይይት ሐሳብ እንደግብዓት አልወሰደም (ለወገራ አውራጃ አስተዳደር ጽ/ቤት ደብዳቤ፣ ቁጥር ጎክ35/43/ጠ ቀን 27/978፤ አቤ ጎበኛ፣ ፲፱፳፱)።

# 5. ማጠቃለያ

ጥናቱ አሽሙር ወይም ምጸትለበስ ሥነግጥሞችን በመሰብሰብ በጎንደር ክፍለሀገር በደርግ አስተዳደር ዘመን ፖለቲካዊና ማኅበራዊ ጉዳዮችን ለማሳየት ሞክሯል። በክፍለ ሀገሩ የሁለት የደርግ ባለሥልጣናት በግጥሞቹ ተዳሰዋል። የሀገሪቱ መሪም እንዲሁ ባንድም ይሁን በሌላ የግጥሞቹ የይዘት አካል እንደሆኑ ማየት ተችሏል። በሥርዓቱ ላይ የነበሩትን የሀገርና የሕዝብ ብሶቶች፣ ምሬትና ሐዘን በኪነቃል ሕዝቡ ሲገልጽ እንደኖረ መረዳት ይቻላል።

ሀገራችን ባላት ሥነምሕዳራዊና ፖለቲካዊ አቀማመጥ የተነሣ ለዓለም ሕዝብ የተለያዩ የሕይወት ፍልስፍናዎችን ስትሰጥም ስትቀበልም ኖራለች። ባንድ ወቅት ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ "… ʻመማርʼ ብቻ ጥቅም የለውም፤ የትምህርት ጥቅሙ የሚታወቀው ለሀገር አገልግሎትና ጥቅም ሲውል ነው" ብለው ነበር። ሆኖም የዘመናዊ ትምህርት ሥርጸት እየሰፋ ሲሄድ ኢትየጵያውያን በሀገረኛ ዕውቀትንና ከውጭ የሚገኘውን አጣጥመው መሄዱን እየተው በተለይ ምዕራባዊያን ኢትዮጵያን የሚያዩበትን መነጽር ሳይጠይቁና ሳይመረምሩ መጠቀም እንዲጀምሩ በር ተከፍቷል። በ20ኛው ክፍለዘመን ሁለተኛ አጋማሽ ወደ ሀገር የገባው አዲሱ የምዕራባውያን የባህል ተጽዕኖ ያስከተለው የፖለቲካ እና ማኅበራዊ አስተሳሰብ ልዕልናና በተለይ የማርክስና ኤንግልስ የፖለቲካ ፍልስፍና "ተማሩ" የሚባሉት ወገኖች የተረዱበት መንገድና አስተምህሮው የሀገሪቱን ዜጎች በታሪኳ አይታው የማታውቀውን አስተሳሰብ በባዕድና ኢሰብዓዊ በሆነ መልኩ ቀይሮታል። ሕዝቧ ከጊዜ ወዲህ "ኋላቀር" ቢባልም የተገዥነትና ለጥቅም ብሎ ነጻነቱን አሳልፎ ለማንም እንደማይሠጥ ጠላቶቹም ይመሰክሩለታል። ስለሆነም ኢትዮጵያን ዓለም የሚያወቃት በበጎ ባህሏና ታሪኳ ነበር። ነገር ግን ለልማት የጎደለውን ሞልታ ልተጠቀምበት አልቻለችም። በተለይ "ተማርኩ" የሚሉትን ወገኖች ክፉኛ ከላይ በተጠቀሰው የውጭ አስተሳሰብ ተጠቅተው ተምረው ሀገር በማልማትና በመመካከር፣ በመተባበር ፈንታ፣ ፀረ አብዮተኛ፣ በራዥ፣ ከላሽ፣ አድኃሪ፣ ተራማጅ፣ ጠባብ ፣አስገንጣይ ፣ትምክህት እየተባባሉ በወገን ላይ ጨካኝነትን፣ በቀልንና አረመኔነትን አዋርሷቸው አልፏል፤ ሀገርንና ሕዝብን በየትኛውም መለኪያ እንደጎዳ ለመረዳት አያዳግትም።

ስለሆነም ጥናቱ የደርግን ሥርዓት ከማየቱ ጎን ለጎን የዘመኑ ርዕዮተ ዓለም በወቅቱ የኢትዮጵያ ጉዳይ ያገባናል የሚሉ ሁሉ ያለ ልማዷ፣ ባህሏና ታሪኳ የተቀበሉት የተዛባ ትርክትና አስተሳሰብ ላላስፈላጊ መስዋዕትነትና መጠፋፋት ዋነኛው ምክንያት እንደሆነ ለመረዳት አያዳግትም።

የነበረው አጠቃላይ ሁኔታ ሀገርን ወደ እድገት ጎዳና ለማምጣት የተደረገውን መስዋዕትነትና መልካም አጋጣሚ ትጋት በተቃራኒው እንዲሄድ አድርጎታል። ካነሳሱም ብስለት እና አስተዋይነት ይጎደለው እንደነበር እንረዳለን። ለምሳሌ፤ ሁሉም የአብዮቱ መሪዎች ተመሳሳይ የፖለቲካ ርዕዮት ዓለም አራማጆች ሆነው ሲጠላለፉ እንጂ ችግራቸውን ሲፈቱ አልታዩም ሀገራቸውን ሲያስቀድሙ አልተስተዋሉም። ኢትዮጵያን ዘንግተው ከአንድነታቸው ይልቅ ልዩነቶችና የስልጣን ጥመኝነትና ግለኝነት ላይ ይሠሩ እንደነበር መታዘብ ይቻላል። በሀገራችን ታሪክ ብዙ የእርስ በርስ ጦርነቶች ነበሩ። አብዮቱን ተከትሎ የመጣው ምስቅልቅል ግን የተለየ እንደነበር መታዘብ ይቻላል። የተቀዳ ከመሆኑ አንጻር አደጋውም የከፋ ሆኖ ተካሂዷል። ከዚህ የታሪክ አጋጣሚ መማር እንደሚያስፈልግ የአጥኝው ጽኑ እምነት ሲሆን፣ በስፋትም ሊጠና ይገባዋል። በጥናቱ ውስንነት የተነሣ ሌሎች ጉዳዮችን በጥልቀት ለማየት አልተቻለም። ሆኖም የሕዝቡን የዕውቀት ምንጭነትና ሁለንተናዊ ልዕልና በዋናነት ትውልዱ ሊማርበት ይገባ ዘንድ በትንሹም ቢሆን ጥናቱ አነሳሽና አመላካች ሊሆን ይችላል። ባጭሩ ታሪክ፣ ባህልና ማንነትን መፈተሽ፣ ማወቅ ሀገርና ሕዝብን እንደሚጠቅም መረዳቱ መልካም ሳይሆን አይቀርም።

# References

Aklilu Habtie.(2017).'*The History of Emperor Haile Silasie I University: The Establishment of Higher Learning Institutions and Expansion'*. Taiwan Printing Press (Original document in Amharic).

Assefa Alemu.(2009). "Analysis of Heroic recitals *(fukkera)* of North Gondar with special focus on Tegede and Armaciho woredas" MA Thesis AAU, Department of Foreign languages and Literature

Atnafu Abate. (1967). 'Letter Written to the Whole Provinces of the Country Number A/D/32/111254/1/154/80 Date 3/6/75 (Original document in Amharic).

Bahru Zewde. (2014).*The Quest for Socialist Etopia: Ethiopian Student Movement c.160-1974*, Addis Ababa University Press,pp.60-66 and 249-280;

Basic Education Campaign .(1973AM). Evaluation of the Status of Basic Education for an Entire Campaign Fifth Round Report, Gondar, page.1-6 (Original document in Amharic).

Birhanu Asress .(2005 AM). Who was the Protagonist to tell?, the December Riot and its Consequence. Addis Ababa University Press (Original document in Amharic).

Birhanu Dinke .(2010 AM). *'The Fire Invention* (Original document in Amharic).

Biruk Alemneh .(2010 AM). 'T*he Ethiopian philosophy: about Zärayakob and Wäldähiwot Narrative Analysis.* (Original document in Amharic).

Dereje Tizazu.(2006AM).*'Pawlos ńońo biography 1934-1992*, Artistic publishing enterprise. (Original document in Amharic).

Ebrahim Damtew. (2018)."History through oral poetry: Peasant Responses to Land Reform and Land Redistribution in Gondar province, 1975-1982", *Northeast African Studies*, Vl.18,Nos.1-2.

Ethiopia First .(1969AM). *'Report on Gondar Province Revolutionary Agitation and Its Consequences,* Gondar Printing Press. (Original document in Amharic).

Fasikaw Sidelil .(2014AM). The sword Generation. Eclipse publisher. (Original document in Amharic).

Feinberg,L.(1967). *Introduction to satire*.Iowa State, University Press.

Fekede Azeze .(2004AM). Culture and development in Ethiopia papers presented in the discussion by Shiferaw Bekele (ed.) *Forum for Social Studies*. (Original document in Amharic).

Fekede Azeze(1993) '*Oral art"* Ethiopian languages and literature journal'. (Original document in Amharic).

Fekre Sellase Wogderess. (2006 AM). *We and the revolution*. Tsehay publishing . Addis Ababa. (Original document in Amharic).

Fentahun Engida .(2006AM). *Historical Records from Early times to the Present* (Original document in Amharic).

Feqade Azeze.(2006). *Ethiopia the Challenge of Democracy from below .Forum for Social Studies*

in Bahru Zewde and Pausewang,Siegfried (ed.)”Oral Literature Depicting the man, His Regime , officials and proclamations” .Addis Ababa. *Forum for Social Studies, Press.*

Feseha Desta.(2008 AM). *The Revolution and my Memories*. Tsehai Publishing. Addis Ababa. (Original document in Amharic).

Gebru Tareke. (2016). *The Ethiopian Revolution: war in the Horn of Africa*. Addis Ababa